አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የጭብጥ ትንተና በየስንብት ቀለማት

ለአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ

በ

መስከረም ኪዳነማሪያም

ጥር፣ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የጭብጥ ትንተና በየስንብት ቀለማት

ለአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ

በ

መስከረም ኪዳነማሪያም

አማካሪ፡-

አየለ ፍቅሬ(ዶ/ር)

ጥር፣ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ምስጋና

በመጀመሪያ ሁሉን ላደረገ ለልዑል እግዚአብሄር ምስጋና ይግባው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ስራዬን ተከታትለው በማየት ላረሙኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር አየለ ፍቅሬ፣

ሁሌም በቀናነት ላስተናገዱኝ የትምህርት ክፍሉ መምህራንና ሰራተኞች እንዲሁም የአይ.ኢ.ኤስ ቤተመፃሕፍት ባለሞያዎች፣

ዘኒና ንግስቲ ከጎኔ ሆናችሁ ስላበረታችሁኝ፣

በመረጃ እጥረት እንዳልቸገር ከጎኔ ላልተለየኝ ለተከበረው ለብርሃነ መስቀል(ጋሽዬ)፣

በእያንዳንዱ እንቅስቃሴዬ ቀና ትብብራቸው ላልተለየኝ የክፍል ጓደኞቼና አሽከርካሪዎች፣

በመጨረሻም በእያንዳንዱ እንቅስቃሴዬ ከጎኔ ለነበሩት ውድ ቤተሰቦቼና ጎረቤቶቼ እንዲሁም እያንዳንዱ ሥራዎቼን በመተየብ ላገዙኝ የጽህፈት ባለሞያዎች ከልብ የመነጨ ታላቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ iv

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 2

1.4 የምርምር ጥያቄዎች ........ 2

1.5 የጥናቱ ፋይዳ ........ 3

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 3

1.7 የአጠናን ዘዴ ........ 3

1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 3

ምዕራፍ ሁለት ........ 5

2. ክለሳ ድርሳናት ........ 5

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 5

2.1.1 የጭብጥ መተንተኛ ንድፈሀሳብ ........ 5

2.1.1 የጭብጥ ምንነት ........ 7

2.1.2 የጭብጥ አይነቶች ........ 9

2.1.2.1 አብይ ጭብጥ ........ 9

2.1.2.2 ንዑሳን ጭብጦች ........ 9

2.1.3 የጭብጥ ባህሪያት ........ 10

2.1.3.1 ሰዋዊነት ........ 10

2.1.3.2 ዘላቂነት ........ 11

2.1.3.3 ወቅታዊነት ........ 11

2.1.4 የጭብጥ መፈለጊያ ዘዴዎች ........ 12

2.1.4.1 በልቦለዱ ርዕስ ........ 13

2.1.4.2 በገጸባህሪያት ንግግርና የእርስ በእርስ ግንኙነት ........ 14

2.1.4.3 በመቼት ገለጻ ........ 15

2.1.4.4 ሀሳብን በመደጋገም ........ 15

2.2 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ........ 15

ምዕራፍ ሦስት ........ 21

3. የመረጃ ትንተና ........ 21

3.1 የስንብት ቀለማት ረጅም ልቦለድ ዐብይ ጭብጥ ........ 21

3.2 የስንብት ቀለማት ረጅም ልቦለድ ንዑሳን ጭብጦች ........ 27

3.2.1 የ “ያ ትውልድ” ስህተቶች ........ 27

3.2.2 የመበዳደል አዙሪት ........ 33

3.2.3 የተስፋ ጭላንጭሎች ........ 44

ምዕራፍ አራት ........ 52

4. ማጠቃለያ ........ 52

የተጠቀሱ ጽሑፎች ........ 54

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት በ2008 ዓ.ም ለህትመት በበቃው የአዳም ረታ “የስንብት ቀለማት” ረጅም ልብወለድ የጭብጥ አቀራረብን ፈትሿል። ልብወለዱ ያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች መሠረታዊነት እንደ ጥናታዊ አነሳሽ ምክንያቶች ተወስዷል። ጥናቱ አይነታዊ ዘዴን ተጠቅሟል። ነገረህላዌን ለመተንተኛነትሲጠቀም፣ መዛግብት ወይም ሠነድ ፍተሻና ጥልቅ ንባብ ደግሞ በመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴነት ተጠቅሟል።ሁለት የመረጃ ምንጮችንም ተጠቅሟል።እነሱም ቀዳማይና ካልዓይ ናቸው።ቀዳማይ የመረጃ ምንጩ ትንተና የሚካሄድበት  የስንብት ቀለማትረጅም ልብወለድ ሲሆን ካልዓይ የመረጃ ምንጮች የምርምር ዘዴ መፃህፍት ፣የንድፈሀሳብና ተዛማጅ ፅሁፎች ናቸው። የልብወለዱን ርዕሰ ማጤን፣ የገፀባህርያትን ምልልስ/ የእርስበርስ ግንኙነት መመርመር፣ የመቼት ገለጻና የሀሳብ ደግግሞሽ  በመረጃ ትንተናው ወቅት ለጭብጥ ትንተናው አገልግሎት ላይ የዋሉ የጭብጥ መፈለጊያ ዘዴዎች ናቸው። የስንብት ቀለማት የጊዜ መቼት ከ1960ዎቹ መጀመሪያ እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ ባሉት የጊዜ ሀዲድ ላይ የተዘረጋ ሲሆን በእነዚህ ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ የተከሰቱት አበይት ሀገራዊ ክስተቶች የ1966ቱ አብዮት፣ የወያኔና የሻዕቢያ ትግል እንዲሁም የሌሎች ተቀናቃኝ ፓርቲዎች የስልጣን ሽሚያ እንደ ልብወለዱ የታሪክ ማስታወሻ ሆነው ቀርበዋል። የመረጃ ትንተናው ሁለት አበይት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የልብወለዱን አብይ ጭብጥ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ንዑሳን ጭብጦችን ይዟል። ሞት ወይም ስንብት የተፈጥሮ ጠባይና አካል መሆኑን ማርዳት የልብወለዱ አብይ ጭብጥ ሲሆን “የ ያ ትውልድ ስህተቶች”፣ የመበዳደል አዙሪትና ጭላንጭል ተስፋዎች ደግሞ እንደ ልብወለዱ ንዑሳን ጭብጦች ተዳሰዋል። የ ያ ትውልድ ስህተቶች በ1960ዎቹና 1970ዎቹ የኖሩ ወጣቶች የፈጸሟቸውን ፖለቲካዊ ስህተቶች ተመልክቷል። የመበዳደል አዙሪት ደግሞ በገፀባህርያት መካከል የነበሩ ቁርሾዎችና ጥሎች የተዳሰሰበት ክፍል ነው። ጭላንጭል ተስፋዎች ደግሞ1960ዎች እና1970ዎቹ ውስጥ የኖሩ ወጣቶች ከፈጸሟቸው ስህተቶች እንዲሁም በዘመኑ ከነበረው ሀገራዊ ቀውስ በኋላ የታየውን አንጻራዊ ሠላምና መረጋጋት እንዲሁም አዳዲስ የለውጥ ጅማሮዎች የተበሰሩበት ክፍል ነው።*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴና የጥናቱ አደረጃጀት የሚሉ ንዑሳን አርዕስቶች ተካትተዋል።

በ2008 ዓ.ም በታተመው የአዳም ረታ "የስንብት ቀለማት" ረጅም ልብወለድ የጭብጥ ትንተና ማካሄድ የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማ ነው።ጥናቱ አይነታዊ ዘዴን ተጠቅሟል። መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው መዝገብ ወይም ሰነድ ፍተሻ ነው።ይህ ጥናት ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል ።እነሱምቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጭ ናቸው።ቀዳማይ የመረጃ ምንጩ የጭብጥ ትንተና የሚካሄድበት የስንብት ቀለማት ረጅም ልቦለድ ሲሆን ፣ካልአይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቱ ርእሰ፡ ጉዳይ ጋር የተገናኙ የምርምር ዘዴ እና ፣የንድፈሀሳብ መፃህፍት እንዲሁም ተዛማጅ ፅሁፎች ናቸው።ጭብጡን ለመተንተን ነገረ ሕላዌ ንድፈሀሳብን ይጠቀማል።«የስንብት ቀለማት» በ8 ሰፋፊ ምዕራፎችና በ44 ንዑሳን ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን በ940 ገጾች ተቀንብቧል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ስነፅሁፍ በርካታዘርፎችአሉት። ከእነዚህም መካከል ስነግጥም ፣ረጅም ልብወለድ ፣አጭር ልብወለድ፣ ተውኔት፣ስነቃል. . .ዋና ዋናዎቹ ናቸው።ከእነዚህ የሥነፅሁፍ ዘርፎች መካከል ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት የሚያደርገው ረጅም ልብወለድ ላይ ነው።ረጅም ልብወለድ በጠበቀ ቁርኝት ና ትስስር እንዲሄድ ህልውናውን የሚያስገኙለት አላባውያን አሉት ከአላባውያን አንዱ የሆነው የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት ጭብጥ ነው።በዚህ መሰረት ጭብጥ በእያንዳንዱ ተደራሲ ተጨምቆ የሚወጣና ደራሲው በልብወለዱ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና መልዕክት ወይም ፍሬ ጉዳይ ነው።የስንብት ቀለማት እስከዛሬ በአማርኛ ቋንቋተፅፈው ከወጡ ልብወለዶች በመጠኑ ትልቁ ነው።ልብወለዶች በዚህ መጠን በሚለጠጡበት ወቅት ደግሞ አንድ ማእከላዊ ጭብጥ ማግኘት በእጅጉ አስቸጋሪ ነው።ልብወለዱ አንድ ወጥ የትረካ አንፃር የሌለውና አንዱ ገፀባህሪያቱ በአንደኛ መደብ ፣ሌላ ጊዜ ደግሞ ደራሲው በሁሉን አወቅ አንፃር የሚተርክበት መሆኑ ስራውን ይበልጥ ፈታኝ ያደርገዋል።ይሁንና ብዙ ማህበራዊ ጉዳይየዳሰሰው የስንብት

ቀለማት እንደሌሎቹ የአዳም ረታ ስራዎች ጥናት ያልተሰራበት በመሆኑ ይሄንን ክፍተት ለመሙላት ይህ ጥናት ጥረት ያደርጋል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደ ጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ይቆጠራሉ።

- በልብወለዱ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከመነጨ ፍላጎት፣
- ልብወለዱ በገሀዱ ዓለም ተደጋግመው የሚታዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮቻችንን በሰፊው የዳሰሰ መሆኑ፣
- የደራሲው የቋንቋ አጠቃቀም ፣ የአቀራረቡና የአተራረኩ እንግዳነት፣ (ይህም ሲባል ሥራው ለትምህርት ደረጃው ይመጥናል አይመጥንም የሚለውን ይመለከታል። የስንብት ቀለማት ካለው ኪናዊ ዋጋ አንጻር በዚህ የትምህርት ደረጃ ለጥናት መመረጡ አግባብ ነው ብዬ አምናለሁ።)

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዐቢይ ዓላማ በ“የስንብት ቀለማት” ረጅም ልብወለድ ጭብጥ ትንተና ማካሄድ ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

- የታሪኩን የቦታና የጊዜ መቼት ከግምት ውስጥ በማስገባት በልብወለዱ ሊነሱ የሚችሉትን ርዕስ ጉዳዮች ማየት፤
- በእያንዱንዱ የታሪኩ ክፍሎች ጎልተው የወጡ ጭብጦችን መለየት፣
- ጭብጡ ከክፍሎቹ መለያ ቀለማት ጋር ያለውን ግንኙነት መተንተንና ማሳየት፤

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ሊመልሳቸው የሚገቡ የምርምር ጥያቄች አሉት።

- በልብወለዱ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?
- በልብወለዱ ውስጥ ጎልተው የታዩት ጭብጦች ምን ምን ናቸው?

- በልብወለዱ ውስጥ በጭብጥነት የተነሱት ጉዳዮች ከልብወለዱ መቼት (ጊዜና ቦታ) ጋር ሲመሳከሩ ምን ያህል እውነትነት አላቸው?

## 1.5 የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል ተብሎ ይታመናል።

- በልብወለዱ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ይነግራል፣
- በልብወለዱ ውስጥ ጎልተው የታዩ ጭብጦች ምን ምን እንደሆኑ ይጠቁማል፣
- በጭብጥ ትንተና ዙሪያ ለሚያጠኑ አጥኚዎች ርዕስ ሊያስገኝ ይችላል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ዋና አላማ በአዳም ረታ "የስንብት ቀለማት" ረጅም ልብወለድ የጭብጥ ትንተና ማካሄድ ሲሆን የሚያተኩረዉ ከልብወለድ አለባውያን መካከል አንዱ በሆነዉ በጭብጥ ላይ ብቻ ነው። ከዚህ አልፎ ሌሎች አለባዉያንን አይነካም።

## 1.7 የአጠናን ዘዴ

ለጥናቱ የተመረጠዉ የአጠናን ዘዴ ዓይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴ ነው። "Qualitative research... does not use quantification but words." (Syed Mohammed, 2010,p.22) ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት የተሰበሰበው መረጃ የሚገለጸዉ በመጠን ወይም በቁጥር ሳይሆን በቃላት አማካኝነት በመሆኑ ነው።በተጨማሪም ያለውይህን አስመልክቶ "በአይነታዊ ምርምር ተመራማሪው የሚያጠናቸው ጉዳዮች ሁሉ በመጠን ይህን ያህል ተዛምዶ ወይም ልይይት (varation) አላቸው ብሎ ያገኛቸውን መረጃዎች በስታስቲካዊ(ቁጥራዊ) ዘዴ አይገልፃቸውም ።መረጃዎቹን ተንትኖየጥናቱንውጤት ለአንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለፃዊ መንገድ ተከትሎ ነው።"ብሏል።(ያለው፣2006፣19)

### 1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴ መዛግብት/ሠነድ/ ፍተሻ ነዉ። ጥናታዊ ጽሑፉ ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮች ተጠቅሟል። እነርሱም ቀዳማይና ካልዓይ ናቸዉ። ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የሚባለው የጭብጥ ትንተና የሚካሄድበት «የስንብት

ቀለማት» ረጅም ልብወለድ ነው:: ካልዓይ የመረጃ ምንጮች የሚባሉት ደግሞ ከጥናታዊ ጽሑፉ ርዕስ ጋር አብረው የሚሄዱ የንድፍ ሀሳብ እና የምርምር ዘዴ መጻሕፍት፣ እንዲሁም ተዛማጅ ጽሑፎች ናቸው።

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ አራት አበይት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ማለትም ስለጥናቱ ማስተዋወቂያ ክፍል ፣ የጥናቱን ዳራ፣ ጥናታዊ ጽሑፉ ለተደራሲያን ሊያስተላልፈው የፈለገው ፍሬ ነገር ወይም የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴ እንዲሁም የጥናቱን አደረጃጀት ያካትታል። በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ክለሳድርሳን ቀርቧል። ማለትም ከጥናታዊ ጽሑፉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንድፈሐሳባዊ ቅኝትና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ተካትቷል። ምዕራፍ ሦስት በአዳም ረታ “የስንብት ቀለማት” በተሰኘው ረጅም ልቦለድ የመረጃ ትንተና የተካሄደበት ክፍል ነው። በመጨረሻም በምዕራፍ አራት ላይ የጥናታዊ ጽሑፉ ማጠቃለያ ቀርቧል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል የቀደምት ጥናቶች የሚዳሰሱበት ፣ፅንሰሃሳባዊ ትንተና፣ እንዲሁም ጥናቱ ለሚካሄድበት ጭብጥ ትንተና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት የሚቀርብበት ምዕራፍ ነው።

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የጭብጥ መተንተኛ ንድፈሀሳብ

ነገረ ህላዌ(EXISTENTIONALISM) ፍልስፍናዊ ዝንባሌ ኖሮት በአውሮፓ በተለይ በጀርመንና በፈረንሳይ ብቅ ያለው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅትና በኋላ ነበር።ነገረ ህላዌ መሠረቱ የተጣለው በጥንታዊቷግሪክ በሶቅራጥስ እንደሆነ ፍሊን(FLYNN)ገልጿል።በአስራዘጠነኛው ክፍለዘመን የዘመናዊዉ ነገረ ህላዌ መሥራች ተደርገው የሚወሰዱት ሶረን ኬየርጋርድ(SOREN KERKEGAARD)ናቸው።

> The Danish thinker Soren Kierkegaard (1813-1855) is believed to be the father of existentials, who polemically rejected Hegelian ideamlism.According to him "truth is subjectivity,the individual is higher than the universal,&eternity is only possible in time."(Dreyfus&Wrathall.2006;p 141)

ነገረ ህላዌ (EXISTENTIALISM) ከሰው ልጅ ህልውና ጋር የተያያዘ ጉዳይ ወይም ሰውን ማእከል ያደረገ ፍልስፍና ነው።ነገረህላዌን በአንድ ቃል ወይም በአንድ ዐረፍተነገር እንዲህ ነው ብሎ ትርጓሜ መስጠት ያስቸግራል።አክሊሉ የአሜሪካ ሄሪቴጅ መዝገበቃላትን ጠቅሶ እንዲህ ይገልፀዋል፦

> A philosophy that emphasizes the uniqueness & isolation of the individual experience in a hostil or indifferent universe, regards human existence as unexplainable & stress, freedom of choise&responsibility for the consequences of ones acts.(Akillilu,2010,P.13)

ከዚህ ገለፃ የምንረዳው ነገረ ህላዌ በዋነኛነት በሰው ልጆች ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን የፍልስፍና ዓይነት ሲሆን ፤ለሰው ልጆች ነገረ ፍጥረት አንዳች ትርጉም ማግኘት እንደማይቻልና ዓለምም ለሰው ልጆች ህላዌ ግድ እንደሌለው አውቀውየራሳቸውን ትርጉም መፈለግ ብሎም ለድርጊቶቻቸው ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው ብሎ የሚያምን ፍልስፍና ነው።

ሚለር በበኩሉ ይህንን ሀሳብ ደግፎ ሌላ ሶስተኛ ልዕለ ተፈጥሮ ወይም እግዚአብሄር እስከሌለ ድረስ የሰው ልጅ በዚህ አለም ውስጥ የራሱን እጣ ፈንታ የመወሰንና የራሱን ትርጉም የመፍጠር መብት እንዳለው አበክሮ ይገልፃል።

> Existentialists believe that because there is no God to conceive of us, we do not have an essential nature or universal values & rules to rely on, thus, the individual is alone &has to choose or is free to make his own values&essence.(Miller,1948,P.148)

ነገረ ህላዌ ከአስር ያላነሱ የፍልስፍናው መገለጫዎችያሉት ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ እውነታ (FACTICITY)፣ነፃነት (FREEDOM)፣ፍርሃት(ANXIETY)፣ከንቱነት (ABSURDITY)፣ቀቢፀ ተስፋ(DESPAIR)፣ሞት (DEATH)እና ድግግሞሽ(REOCCURRENCE)ዋናዋናዎቹ ናቸው።ይሉናል እነ ድሪፊውስ ።እነዚህ መገለጫዎች ተነጣጥለው የሚታዩ ሳይሆን እርስበእርሳቸው የሚደጋገፉና አንዱ ወደ አንዱ የሚወስዱን ደረጃዎች ናቸው። እውነታ (FACTICITY)በዚህ ዓለም ውስጥ ስንኖር የማንቀይራቸው ሞትን የመሰለ መራራ እውነታዎች መኖራቸውን እንዲህ አይነት ሁነቶችን እንዳሉ ከመቀበል በስተቀር ምንም የማድረግ ስልጣን እንደሌለን ያትታል።ይህ አመለካከት ታዲያ ነፃነት (FREEDOM)ወደሚባለው ሌላኛው መገለጫ ይመራናል ።ነፃነት ስንልም የሰውልጅ ሞትን የመሰሉ መራራ እውነታዎች መኖራቸውን ማወቁም ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንኳየራሱን እጣ ፈንታ በራሱ የመወሰንና እንዳሻው የመኖር መብት እንዳለው እንዲያውቅ ያደርጋል ።ታዲያ ይሄ ገደብ የለሽ የሚመስል ነፃነት ደግሞ በህይወት ላይ ትርጉም እንዲያጣና ሁሉም ነገር ከንቱ (ABSURD) ነው ወደሚል ድምዳሜ ይወስደዋል።ይህ ሕይወት አላፊ ጠፊ መሆኗን ማወቁ ደግሞ ከፍተኛ ወደ ሆነ ፍርሃት (ANXIETY) ውስጥ ይከተዋል።በዚህ ወሰን የለሽ(INFINITE) ዓለም ውስጥ ሙዋዕቲ(FINITE)መሆኑን ማወቁም ከፍተኛ የሆነ ፍርሃት ይፈጥርበታል።ይህም ፍርሃት ከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ(DESPAIR) ውስጥ ይጥለዋል።ከተስፋ መቁረጥ በኋላ የሚመጣው አይቀሬው ሞት (DEATH)ነው።ይህም የነገሮች ሁሉ መቋጫ ተደርጎ ይታመናል ።ታድያ ይሄ ሁሉ አዲስ ነገር ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ሲደጋገም የኖረ የተፈጥሮ ሂደት ነው።ይህም አስተሳሰብ

ድግግሞሽ(REOCCURRENCE) ተብሎ ይጠራል:: ሲሉ ያጠቃልላሉ::(DREYFUS &WRATHALL,2006, P.270-280)

የነገረ ህላዌ (EXISTENTIALISM) ፍልስፍና አቀንቃኞች ከፈረንሳይ ጂን ፓል ሳርተር (JEAN POUL SARTRE)፣አልበርት ካሙስ(ALBERT CAMUS)፣ገብርኤል ማርሴል (GABRIEL MARCEL) እና ሲሞን ዲ ቤቮር(SIMON DE BEAUVOIR) ሲሆኑ ከጀርመን ፍሬድሪክ ኒቼ(FRIEDRICH NIETZSCHIE)፣ካርል ጃስፐርስ(KARL JASPERS)እና ማርቲን ሄድጋር(MARTIN HEIDEGGAR)፣

ፊዮዶር ዶስቶብስኪ(FYODO DOSTOEVSKY)፣ፍራንዝ ካፍካ(FRANZ KAFKA) እና ሳሙኤል ቤኬት (SAMUEL BECKETT) ናቸው:: (THOMAS,2006,P.63)

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት የሆነው የስንብት ቀለማት ከዚሁ ፍልስፍናጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ያያል::

### 2.1.1 የጭብጥ ምንነት

የጭብጥን ምንነት አስመልክቶ ሁሉንም ምሁራን የሚያስማማ አንድ ወጥ ብያኔ ባይኖርም እንኳ እነ ሬኔ ዌሌክ እነ አውስቲን ዋረን እነ ካትሪን ና ካርልሰንን የመሳሰሉ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰንዝረዋል:: ከዚህ በማስከተልም የጭብጥን ምንነት አስመልክቶ የተሰጡ ብያኔዎች ከተጨማሪ ማብራሪያዎች ጋር ይቀርባሉ::

እነሬኔ እና አውስቲን የጭብጥን ምንነት አስመልክቶ "the central idea or underlying meaning of a workofliterature... thekeyto understanding a work of literature" (Rene&Austin,1992,p.192-193) ጭብጥን በተመለከተ የድርሰት ማዕከላዊው ሀሳብ እንደሆነ ገልጸው ጭብጥ ልብወለድን በመረዳት ሂደት ቁልፉን ሚና እንደሚጫወት ያትታሉ:: ትሪመርና ጄኒንግስም የጭብጥን ምንነት በተመለከተ ከነረኔ ወሌክ ብያኔ ጋር ተዛማጅነት ያለው ሀሳብ ይሰነዝራሉ:: Trimmer and Jennings ጭብጥን "the key to understanding a story" (p. 13) በማለት ይገልጹታል:: ጭብጥ ድርሰትን በመረዳት ሂደት ቁልፍ ሚና አለው:: በአንድ ድርሰት ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ የድርሰቱን ጭብጥ ወይም ማዕከላዊ ሀሳብ መረዳት ዋናውን ድርሻ ይይዛል::

ካትሪን ደግሞ ሉከንስን ጠቅሳ "A theme is a central meaning or idea that holds a story together."(Kathryn,1992,p.86) በሉከንስ ብያኔ መሰረት ጭብጥ የሚባለው የልብወለዱ ማዕከላዊው ሐሳብ ወይም ታሪኩን አዋድዶ የሚይዘው አላባ ነው::

> ካትሪን አሁንም ሉከንስን ጠቅሳ In storytelling “what happened next?” is a question about chronological and narrative order. “why did it happened?” is a question about conflict and plot. But when we ask, “what does it all mean?” we begin to discover theme.(Kathryn,1992,p.87)

ሉከንስ «ከዚያስ ቀጥሎ ምን ሆነ?» የታሪክ ጥያቄ ነው፤ «ለምን ሆነ?» ስንል የግጭት ወይም የሴራ ጥያቄ ነው፤ «ይሄ ሁሉ ስለምንድን ነው?» ካልን ግን የጭብጥ ጥያቄ ነው ይለናል፡፡ ካርልሰን ደግሞ በጭብጥና በመልዕክት መካከል መጠንኛ ልዩነት እንዳለ ይገልጻል፡፡

> Theme should not be confused with message as though the values of a story to be measured by how large and strong are the does moral medicine it ladles out to the reader. There may be a moral lesson, of course there often is in the most famous works of literature. Many stories contain no explicit statement of theme. In fact the more artistic stories often avoid making abstract statement to sum up their theme. Theme its basic subject, if it is good will have unity conference and total meaning and this we may allied its theme. ( Carlson ,1979,p.20)

ካርልሰን ጭብጥና መልእክት ሁለት የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑና በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሊያምታታን እንደማይገባ ይገልጻል፡፡ ጭብጥ ስንለይም ከሚያበረክቱልን ስነምግባራዊ ፋይዳ አኳያ መሆን የለበትም፡፡ ይህ ሲባል ግን ጭብጥ ሞራልን በማረቅ ረገድ ምንም አይነት አስተዋጽዖ የለውም ማለት አይደለም፤ ለዚህ ዓላማ ታስቦ አይጻፍም ለማለት እንጂ፡፡ እስካሁን ከተብራሩት ብያኔዎች ለመረዳት እንደሚቻለው ጭብጥን በተመለከተ ሁለት አይነት እሳቤ አለ፡፡ አንደኛው፣ «ጭብጥ የሚባለው አንባቢያን ከልብወለዱ የሚወስዱት ማዕከላዊ መልዕክት ነው» የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ጭብጥ እና መልዕክት አንድ አይደሉም፡፡ «ጭብጥ የሚባለው ልብወለዱ ስለምንድን ነው የሚተርከው?» ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ነው የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ ታድያ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የሚከተለው የትኛውን እሳቤ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ጥናቱ በዋናነት፣ በአንደኛው ሐሳብ ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡

## 2.1.2 የጭብጥ አይነቶች

እንደየሀገሩ የስነ ጽሁፍ ፈለግ እንዲሁም እንደ ደራሲያኑ ዝንባሌ ልዩ ልዩ አይነት የጭብጥ አይነቶች እንዳሉ ሲነገር እንሰማለን። ካርልሰን በአንድ ልብወለድ ውስጥ አራት አይነት ጭብጦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያስረዳል። እነዚህም የጭብጥ አይነቶች አለምአቀፋዊ ጭብጦች (UNIVERSAL THEMES)፣ አርኪታይፓል ጭብጦች (ARCHETYPAL THEMES)፣ ታሪካዊ ጭብጦች (HISTORICAL THEMES) እና ግለሰባዊ ጭብጦች (PERSONAL THEMES) በመባል ይጠራሉ።(CARLSON,1979,P.2)

«በአንድ ልቦለድ ዉስጥ የማዕከላዊ ሃሳብነት ደረጃቸዉ የተለያዩ ጭብጦች ሊገኙ ይችላሉ። ልብወለዱ ለዋናዉ ታሪክ መተረክ ምክንያት የሚሆን አንድ ዓብይ ጭብጥና እሱን የሚያደምቁ ወይም የሚያጎሉ ሌሎች ንዑሳን ጭብጦች መያዝ ይችላል።» ብሏል። (ዘሪሁን፣1992፣185)ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በሀገር ውስጥ በተጻፈ ልብወለድ ድርሰት ላይ እንደማተኮሩ መጠን በሀገር ቤቱ በሚታወቀው የጭብጥ አደረጃጀት ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል።

### 2.1.2.1 አብይ ጭብጥ

አብይ ጭብጥ የሚባለው በአንድ ልቦለድ ዉስጥ ሊተላለፍ የተፈለገዉ ዋና መልእክት ነው። ይህን አስመልክቶ ዘሪሁን«አንድ ደራሲ ህይወትን በትክክል መቅረጽ ከቻለ፣ የህይወትን እዉነታ በጉልህ ካሳየ፣ ስለህይወት አንድ ትልቅ ሀገር በቀል እሳቤ ካቀረበ ወይም ታሪኩ ሁሉን የሚያስተሳስር ዋነኛ ሃሳብ እንዲይዝ ካደረገና ይህንንም በልቦለድ ዉስጥ ካንጸባረቀ ልቦለዱ ዓብይ ጭብጥ አለዉ ይባላል።» ብሏል(ዘሪሁን፣1992፣185)። ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በአንድ ልቦለድ ውስጥ ሁሉንም ታሪክ የሚያስተሳስረው ዋና ሀሳብ የልቦለዱ ዓብይ ጭብጥ ይባላል። ይህም ጭብጥ ሕይወትን በትክክል መቅረጽና የሕይወትን እውነታ በጉልህ ማሳየት ይገባዋል።

### 2.1.2.2 ንዑሳን ጭብጦች

ንዑሳን ጭብጦች በልቦለዱ ዉስጥ ሊተላለፍ የተፈለገዉን መልዕክት ወይም ዓብይ ጭብጥ የሚያደምቁና ከራሱ ከዋናው ጭብጥ የሚመዘዙ ናቸዉ። በመሆኑም ዓብይና ንዑሳን ጭብጦች በአንድ ልቦለድ ዉስጥ ተሳስረዉና ተቆራኝተዉ የሚጓዙ እንጂ የሚነጣጠሉ አይደሉም። ይህንን ሃሳብ በመደገፍ «ዓብይና ንኡሳን ጭብጦች በታሪኩ ዉስጥ ተነጣጥለዉ የሚኖሩ አይደሉም። በመካከላቸዉ የጠበቀ ቁርኝት አላቸዉ። አንዱ ወደ ሌላዉ ያንደረድራል። ንኡሳን ጭብጦቹ በዓብይ አንድ ላይ ይተሳሰራሉ።››ይላሉ። (ዘሪሁን፣1992፣185)

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ንኡሳን ጭብጦች ከአብይ ጭብጥ የሚመዘዙ ሲሆን በልብወለድ ውስጥ ያላቸው ሚናም አብይ ጭብጡን ማጉላትና ማድመቅ ነው፡፡

## 2.1.3 የጭብጥ ባህሪያት

ካርልሰን "Themes give us a way to understand the world around us and our place in it" (Carlsen,1979,p.12). የአንድ ልብወለድ ድርሰት ጭብጦች በዙሪያችን ስላለው ዓለምና በዓለሙ ውስጥ ስላለን ቦታ መጠነኛ የሆነ ግንዛቤ ይሰጡናል፡፡

ጭብጥ እንደማንኛዉም የልቦለድ አላባ ከሌሎች አላባዊያን ተለይቶ የሚታወቅበት ባህሪያት አሉት፡፡ የጭብጥ ባህሪያት የሚባሉት ሰዋዊነት፣ ዘላቂነት እና ወቅታዊነት ናቸው፡፡ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተብራርተዋል፡፡ እኒህ ባህሪያት አንድን ሐሳብ ጭብጥ ነው ብሎ ለመደምደም እንደ መስፈርት ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

### 2.1.3.1 ሰዋዊነት

ልቦለድ የገሀዱ አለም ነጸብራቅ የሆነ የፈጠራ ስራ ነዉ፡፡ ይህ የፈጠራ ስራ የሚመነጨዉም ከሰዉ ልጅ ሕይወት ነው፡፡ ልቦለዱ ከሰዉ ልጅ የእለት ተእለት ገጠመኝ የተቀዳ የእዉኑ አለም ነጸብራቅ ከሆነ የሚያስተላልፈው መልዕክትም የሰዉን ልጅ ፍላጎት፣ ባህሪ፣ ስሜትና አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ይህን በተመለከተ ፦

> ጭብጥ ምንጊዜም ሰዋዊ ቢሆን ይመረጣል፡፡ የሰዉን መሰረታዊ ባህሪያት እያሚንጸባርቅ፣ ሰዉ ከተፈጥሮና ከማህበራዊ አካባቢዉ ያለዉን ግንኙነት እሚነካ የሰዉ ልጅን የአኗኗር ስርዓትና ለመኖር ሲል የሚፈጥራቸዉን አይቀሬ ግንኙነቶች የሚጠቅስ ሲሆን ሰዋዊነቱም የጎላ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ሃያሲያን የአንድን ልቦለድ ታላቅነት የሚመዝኑት በጭብጡ ሰዋዊ መሆን ነዉ፡፡(ዘሪሁን ፣1992፣185)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳዉ በልቦለዱ አለም ዉስጥ የሚሳሉት ገጸባህሪያት የሚያደርጉት አጠቃላይ የህይወት እንቅስቃሴ የገሀዱ አለም ሰዎች ከሚያደርጉት ድርጊት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት የሚል ነው፤ ስለዚህ ያልተደረገዉን፣ ያልተሰማዉን፣ ያልታየዉን ሰዎች

የማያደርጉትን ድርጊት ገጸባህሪያት በልቦለዱ ዉስጥ ቢያንጸባርቁ በአንባቢያን ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ልቦለድ ሰዋዊ እንዲሆን ከተፈለገ መልዕክቱም የሰዉን ባህሪ እንዲይዝ ደራሲዉ የሰዉ ልጅ የሚሰራዉን፣ ያየዉንና የሰማዉን በልቦለድ ዉሰጥ ማካተት አለበት ማለት ነው።

## 2.1.3.2 ዘላቂነት

አንድ ደራሲ በየትኛዉም ዘመን እና ቦታ ሊነበብ የሚችል ስራ ሲያቀርብ ተቀባይነቱ ላቅ ይላል። ምክንያቱም ጭብጡ በአንድ ወቅት ታይቶ የሚጠፋ ሳይሆን ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ከዘመን ወደ ዘመን የሚሸጋገር በመሆኑ ነው። ይህን አስመልክቶ ዘሪሁን የሚከተለውን ብሏል። "ዘላቂነት ማለት ድርሰቱ ዘመንና ቦታዉን ጥሶ በየትኛዉም ዘመን ሊነበብ ሲችል ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት ነዉ። የተጻፈበትን ዘመንና ክልል ዘሎ የአንባቢያንን ልብ መሰረቅ ከቻለ ዳግም ለስራዉ ትልቅነት አንድ ምስክርነት ተገኘ ማለት ነዉ።"(ዘሪሁን፣1992፣185-186)

## 2.1.3.3 ወቅታዊነት

በየትኛውም ጊዜና ቦታ ቢነበቡ ኪናዊ ዋጋቸው የማይቀንስ ዘላቂነት ያላቸው ጭብጦች እንዳሉ ሁሉ፣ ከተጻፉበት የዘመን አድማስ ተሻገረው መሄድ የማይችሉ ወቅታዊ ጭብጦችም አሉ። "ደራሲ በአንድ ወቅት በአንድ በተወሰነ አካባቢ ብቻ የተፈፀመ ጉዳይን ለማንፀባረቅ የሚያመጣቸው ፣እውነትነታቸው ለወቅቱና ለቦታው ብቻ የሆኑ ጭብጦች ናቸው።ወቅቱም ካለፈ የአንባቢን ልብ የማይሰርቁና ተረስተው ሊቀሩም የሚችሉ ናቸው።(ዘሪሁን ፣1992፣186)ከዚህ ጥቅስ የምንረዳውበጊዜው ተፈጥሮ በነበረ ዘመን አመጣሽ ወረርሽኝ ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ በጊዜው በነበረው ፖለቲካዊ ርዕዮት ዓለም ጫና፣ ወይም ደግሞ ዘመኑ በሚከተለው የአጻጻፍ ስልት (ፋሽን)፣ ወይም ደግሞ በዘመኑ በተከሰተ ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ (የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ጎርፍ፣ እሳተ ገሞራ፣ የመሬት መንሸራተት፣ ጦርነት፣... ወዘተ) አማካይነት ለማስታወሻነት ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ለፕሮፖጋንዳ ታቅደው የሚጻፉ ልቦለዶች ጭብጥ አብዛኛውን ጊዜ የወቅታዊነት ባህሪ ይታይባቸዋል። ለአብነት ያክል በሰማንያዎቹ መጨረሻና በዘጠናዎቹ መጀመሪያ የታተሙ ሥራዎችን መመልከት ይቻላል። በዘጠናዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ኤች. አይ.ቪ ቫይረስ አዲስ አበባ ውስጥ ክፉኛ የተስፋፋበት ወቅት ነበር። በርካታ ቁጥር ያላቸው የቫይረሱ ተጠቂዎች ቁጥር የተመዘገበበት ወቅትም ነበር ይባላል። በወቅቱ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ የልቦለድና የግጥም ሥራዎች እንደ አሸን ፈልተው ነበር። ይሁን እንጂ የግጥምና የልብወለድ ሥራዎችን ዛሬ ላይ ሆነን ስናነባቸው ልክ እንደበፊቱ

ለዛና ጣዕም የላቸውም፡፡ በተመሳሳይ በስልሳዎቹና በሰባዎቹ ይታተሙ የነበሩ የፈጠራ ሥራዎችን መመልከት ይቻላል፡፡ ታድያ ለአያሌ ዓመታት ከማንነታችን ጋር ተቆራኝቶ የኖረውን ዘውዳዊ ሥርዓት በአንድ ጀንበር ከሕዝቡ አዕምሮ ላይ ጠራርጎ ማውጣት ቀላል ሥራ አልነበረም፡፡ ሕዝቡ የተፈጠረውን ለማመን ከመቸገሩ የተነሳ ንጉሡ ተመልሰው ይመጣሉ የሚሉ  አሉባልታዎች ጭምር ይነዙ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ በዘመኑ የነበሩ ጸሐፊያን የአብዮቱን መልካም ጎኖች የሚያሳዩና የዘውዳዊዉን ሥርዓት አስከፊነት የሚገልጹ በርካታ የልብወለድና የግጥም ሥራዎችን አሳትመዋል፡፡ በዚህ ዘመን ከተነሱ እንዲሁም ለሀገራችን የሥነጽሑፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ካበረከቱ ደራሲያን መካከል በዓሉ ግርማ አንዱ ነው፡፡ ስድስት በሰፊው የተነበቡ ሥራዎችን አበርክቷል (**ከአድማስ ባሻገር፣ የሕሊና ደወል፣ ሀዲስ፣ ደራሲው፣ የቀይ ኮከብ ጥሪ፣ ኦሮማይ**)፡፡ ከእነዚህ የደራሲው ሥራዎች ውስጥ ዛሬም ድረስ በሰፊው እየተነበቡ የሚገኙት **ከአድማስ ባሻገር** እና **ኦሮማይ** ብቻ ናቸው፡፡ ለዚህ በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሰው ደግሞ ያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ **የሕሊና ደወል** እና **ሀዲስ**ን ብንመለከት ስለ ትምህርትና ሥራ አስፈላጊነት የሚተርኩ ልቦለዶች ናቸው፡፡ የቀይ ኮከብ ጥሪ ደግሞ አብዮቱ ስለሚገጥመው ፈተናና በመንግሥት በኩል መሰራት ስላለባቸው ሥራዎች የሚተርክ ነው፡፡ እኒህና መሰል ለፕሮፓጋንዳ ዓላማነት የተደረሱ ሥራዎች ወቅታዊ ጭብጥ ላላቸው ልብወለዶች ሁነኛ ማሳያ ናቸው፡፡

### 2.1.4 የጭብጥ መፈለጊያ ዘዴዎች

የአንድ ልብወለድ ማዕከላዊ ሐሳብ ወይም መልእክት በቀላሉ አይገኝም፡፡ ጭብጥ፣ የአንባቢዉን ጥበባዊ የምርምርና የትንተና ችሎታ የሚጠይቅ ሥራ ነው፡፡ የአንድን ልብወለድ ጭብጥ በተለያየ መንገድ ልናገኘው እንችላለን፡፡ የልቦለዱን የታሪክ መዋቅር በመመርመር የልቦለዱ ጭብጥ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡ እነ ግሪግ ጆንሰንደግሞ ጭብጥን ለማግኘት እንዲህ ይሉናል፦

> Discovering &stating the theme of a story is often a delicate task.Sometimes we will feel what the story is about strongly enough&yet find it difficult to put this feeling into words. . . .There is no prescribed method for discovering theme.Sometimes we can best to get at it by asking in what way the main character has changed in the course of the story and what if anything, the character has learned before its

end .Sometimes the best approach is to explore the nature of the central conflict and its outcome.Sometimes the title will provide an important clue.( Grig& Jhonson,2012 ,p.196)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አንድን ጭብጥ ለማውጣት መንገዱ አልጋ በአልጋ እንዳልሆነና ፤ይሄ ነው የሚባልም ዘዴ እንደሌለ ፣ጭብጡን ለማውጣት ግጭቱንና ግጭቱ ያስከተላቸውን ውጤቶች እና ርዕሱ የሆነ ጥቆማ ሊሰጡን እንደሚችሉ ነው።

> The meaning of the work is not what the author had in his mind at some point, nor is it simply a property of the text or the experience of a reader. Meaning is an inescapable notion because it is not something simple or simply determined. It is simultaneously an experience of a subject and a property of a text. It is both what we understand and what in the text we try to understand.(Jonathan19 97,p.167)

በጆናታን ማብራሪያ መሠረት ደግሞ የአንድ ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብ የሚባለው፣ ደራሲው ያወጣ ያወረደው ወይም መጽሐፉ የያዘው ቀምነገር አልያም አንባቢው ተረዳሁት የሚለው ፍሬ ነገር አይደለም። ምክንያቱም የጽሑፉን ፍሬ ነገር በቀላሉ መረዳት አዳጋች ነው። የጽሑፉ ፍሬ ነገር ጠጣር ነው፤ የጽሑፉ ፍሬ ነገር የሚባለው፣ አንብበን የተረዳነውና ለመረዳት እየሞከርነው ያለው ነገር ድምር ነው።

ጭብጥን ከልቦለድ ውስጥ ጨምቆ ለማውጣት ራሱን የቻለ ቀመር የለም። ነገር ግን በውል የታወቀ ዘዴ ባይኖርም ጭብጥ ለማግኘት በታሪኩ ውስጥ የትኛው አካባቢ ቢተኮር ፍንጭ ማግኘት እንደሚቻል መናገር ይቻላል። የአንድ ልቦለድ ጭብጥን ለማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር ጠቃሚ ነው።

## 2.1.4.1 በልቦለዱ ርዕስ

ደራሲያን ለልቦለዱ በሚሰጡት ርዕስ የተደራሲያንን አቅጣጫ በማስያዝ መልዕክታቸዉን እንዲረዱ ያደርጋሉ። በዚህ ሁኔታ የልቦለዱ ርዕስ የጭብጥ ማቅረቢያ ቴክኒክ በመሆን

ያገለግላል። "ደራሲዉ ብዙን ጊዜ ለልቦለድ ርዕስ ሲሰጥ በትንሽ ቃላት በመጽሀፉ ዉስጥ ያሉትን በጣም አስፈላጊና ቁም ነገር አዘል የሆኑ ነገሮችን አጠቃሎ ሊያስቀምጥ ስለሚችል የልቦለዱ ርዕስ ጭብጡን ለማግኘት ፍንጭ ይሰጠናል። የልቦለዱ ርዕስ የጭብጥ መነገሪያ ዘዴ ነዉ ሲባል ግን ሁልጊዜ ርዕሱ የልቦለዱን ጭብጥ ያሳያል ወይም ወደ ጭብጥ ይመራል ማለት አይደለም። የአንዳንድ ልቦለድ ጭብጥ ከርዕሳቸዉ ጋር ምንም አይነት ቁርኝት የሌላቸዉ ሊሆኑ ይችላሉ።"(ዘሪሁን፣1992፣186)

## 2.1.4.2 በገጸባህሪያት ንግግርና የእርስ በእርስ ግንኙነት

ደራሲያን ማስተላለፍ የሚፈልጉትን ጭብጥ በሚፈጥሯቸዉ ገጸባህሪያት እና በሚገቡባቸዉ ግጭቶች አማካኝንት ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ይህን በተመለከተ ዘሪሁን እንደሚከተለዉ ይገልጸዋል።

> አብዛኛዉን ጊዜ በዋና ገጸ ባህሪያቱ ሰብዕናና እንቅስቃሴ ላይ ማንዣበብ ጠቃሚነት አለዉ። የገጸባህሪያቱ አጠቃላይ ሰብዕና፣ ገጸባህሪያቱ የሚገቡባቸዉ ሁነቶችና በነዚህ ሁነቶች ዉስጥ የሚፈጽሟቸዉ ድርጊቶች፣ድርጊቶቹ የሚያስከትሏቸዉ ዉጤቶች፣ በታሪኩ ዉስጥ የሚፈጠሩ አብይ ግጭቶች እነሱም የሚያስገኟቸዉ ዉጤቶች መጤን አለባቸዉ። በተጨማሪ ዋና ዋና ገጸባህሪያቱ ከሌሎች ገጸባህሪያት ያላቸዉ ግንኙነቶች በተራኪዉ ስለህይወት የሚሰጡ አስተያየቶችና ትርጓሜዎች እንዲሁም አበይት ሁነቶች ርስበርስ ተሻሩርበዉ የሚያመጡትን ዉጤት መመርመር ወደ ጭብጡ ሊመሩ ይችላሉ።የገጸባህሪያት ንግግርም ጭብጡን ለማግኘት ሊረዳ ይችላል። (ዘሪሁን፣2004፣187)

ከዚህ ገለጻ የምንረዳዉ ደራሲዉ በገጸባህሪያት ንግግር ወይም ግንኙነት አማካኝነት ጭብጡን ሊያስተላልፍ እንደሚችል እንረዳለን።

### 2.1.4.3 በመቼት ገለጻ

"The setting refers to where &when a story takes place.the setting includs physical environment this includes the geographic location (eg. Country,City),thenaturalenvironment(eg.,forest,mountaintop or desert), bu ilidinigs,furniture ,clothes,sounds,smells&weather.Socialenvironment this includes manners,customs,social class&atmosphere or mood,time. . . . The setting is very important to the story.Authors use setting to develop themes . . . . . (William, 1996, p.2)

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው መቼት ማለት የልቦለድ ታሪክ የሚፈጸምበት ቦታና ጊዜ ሲሆን በዉስጡ በርካታ ነገሮችን ይይዛል።አንድ ልብወለድ የቀረበበት ዘመን ፣መልክአምድሩ ፣የማህበረሰቡ ኢኮኖሚ፣አልባሳቱ ፣ባሕሉና አጠቃላይ ነባራዊዉ ሁኔታ በልቦለዱ መቼት ውስጥ ይጠቃለላሉ ።መቼት በልብወለዱ ውስጥ ከሚፈፀመው ታሪክ ጋር አብሮ የሚሄድና የተፃፈበትን ጊዜና ቦታ በመገንዘብ የልብወለዱን ጭብጥ መገመት እንደሚያስችል ነው።

### 2.1.4.4 ሀሳብን በመደጋገም

አንድን ሃሳብ በልቦለዱ ዉስጥ ያሉ ገጸባህሪያቶች በተደጋጋሚ ሲደጋግሙት ከሰማናቸዉ የጭብጥ ትኩረታችን በዚህ ላይ ከሆነ ፍለጋችን ሊሳካ ይችላል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ደራሲያን በልቦለዳቸዉ ዉስጥ ማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት በገጸባህሪያት አማካኝነት እንዲደጋገም ሲያደርጉት ይታያል፡፡ ‹‹በልቦለዱ ዉስጥ በተለያዩ ገጸባህሪያትም ሆነ በተራኪዉ በተደጋጋሚ ሁነቶች ዉስጥ የሚገኙ ሃሳቦች ጭብጥ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን እንድንጠረጥር ያደርጉናል፡፡ አንድ ሃሳብ በዋና ገጸባህሪዉና በሱ ዙሪያ በሚኖሩ ሌሎች ገጸባህሪያት ተዘዉትሮ ሲነገር ከሰማነዉ የጭብጥ ትኩረታችንን በሱ ላይ ብናደርግ ፍለጋችን ሊሳካ ይችላል፡፡››(ዘሪሁን፣1992፣187) ከዚህ ሐሳብ እንደምንረዳዉ ደራሲያን ማለት የፈለጉትን ጉዳይ በተደራሲያን ላይ ተቀርጾ እንዲቀር እንዲደጋገም ሊያደርጉ እንደሚችሉ እንገነዘባለን፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት አላቸው ተብሎ የታመነባቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ የተጠኑ አራት ጥናታዊ ጽሑፎች ተዳስሰዋል።

በቀዳሚነት በተዛማጅነት የተዳሰሰው ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል እ.ኤ.አ በ2010 የትምህርት ዘመን በአክሊሉ ደሳለኝ ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበው «ኤግዜስቴንሽናሊዝም በተመረጡ የአዳም ረታ ሥራዎች» Existentialism in the selected creative works of Adam Reta) የሚለው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው:: ለጥናቱም ከደራሲው ስራዎች ውስጥ ግራጫ ቃጭሎች (ረዥም ልቦለድ)፣ ከማህሌት የአጫጭር ታሪኮች መድበል("ኤልዛቤል"፣ "ሲፊንክስ"፣ "ከልጅቷ"፣ "የአበቦች ታሪክ" እና "የድንች መሰዋዕት") የተመረጡ ሲሆን ከእቴሜቴ ሎሚ ሽታ የአጫጭር ታሪኮች መድበል ደግሞ ራሱ "እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" ተመርጧል:: ጥናቱ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅትና ከጦርነቱ ማግስት ገንኖ በወጣው ፍልስፍና ኤግዝስቴንሽናሊዝም (Existentialism) ላይ የተመሠረተ ሲሆን በአዳም ረታ የተመረጡ ሥራዎች ላይ የዚህ ፍልስፍና መገለጫዎችን ማሳየት፣ ከሕይወት ከንቱነት (Absurdity) ፍልስፍና አመንጪ አልበርት ካሙ (Albert Camus) ሥራ ሲስፈስ ጋር ያላቸውን ተመሳስሎ መጠቆም፣ የደራሲውን ሐይማኖታዊና ፍልስፍናዊ አተያይ መመርመር የጥናቱ ዓላማዎች ናቸው:: ፍልስፍናው በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅትና ጦርነቱ ማግስት አውሮፓ ውስጥ በተከሠተ ታላቅ ስነልቦናዊ መረበሽ ምክንያት የመነጨ ሲሆን የሰው ልጅ ያለ ምክንያት የተፈጠረ፣ ያለ ምክንያት የሚሰቃይና እንደተሰቃየ የሚሞት ከንቱ ፍጥረት መሆኑን ይገልጻል:: አልበርት ካሙ ይህንን የሰውን ልጅ ከንቱነት «አብዘርዲቲ» ተብሎ በሚጠራው «የኤግዚስቴሽናሊዝም» አንዱ መገለጫ ላይ የሰውን ከንቱ ፍጥሩነት ከግሪኩ ከንቱ ጀግና (Absurd Hero) ጋር ያመሳስለዋል:: የፍልስፍናው አቀንቃኞች የሰው ልጅ መፈጠሩም ዋጋ ቢስና መጨረሻው ሁልጊዜም በሞት የሚደመደም ፍጡር ነው ብለው ያምናሉ:: ይህን ከንቱነት አልበርት ካሙ ከግሪኩ የአፈታሪክ ተኮናኝ ሲስፈስ ጋር ያመሳስለዋል:: የአልበርት ካሙ የሰውን ልጅ ግብየለሽ ሕይወት ያለግብ ድንጋይ እንዲገፋ አማልክቱ ከፈረዱበት የግሪኩ «ሲስፈስ» ጋር አመሳስሎታል:: ፍልስፍናው የገነነው በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ነው:: ጦርነቱ ያስከተለው ቀውስ ለፍልስፍናው መስፋፋት ዋነኛ ምክንያት እንደነበር የዘርፉን ምሁራን ጠቅሶ አብራርቷል ::

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረት የሆነው «የስንብት ቀለማት» ከዚሁ ፍልስፍና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ያቅፋል:: በስንብት ቀለማት ውስጥ የተካተቱት አያሌ ገጸባህርያት ከላይ ከላይ ስናየቸው ጥሩና መጥፎ የፍቅር ታሪካቸውን የሚያጫውቱን ቢመስልም ቅሉ ጠለቅ ብለን ስንመረምራቸው ከተራ የፍቅር ታሪክም በላይ መሆናቸው ይገለጥልናል:: ጊዜው ሀገሪቱ ማጥ ውስጥ የገባችበትና ስር የሰደደ የፖለቲካና የባህል ለውጥ የተሰተናገደበት ወቅት ነበር::

ይህም ሀገራችን በሁለተኛው ዓለም ጦርነትና በጦርነቱ ማግስት አውሮፓ ካስተነገደችው ቀውስ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሁኔታ ውስጥ ነበረች። ይህም ዜጎች ለተመሳሳይ የኤግዝስቴንሽናሊዝም ፍልስፍና መገለጫዎች (ተስፋ ሙቀረጥ (Despair)፣ ፍርሐት (Anxiety)፣ ከንቱነት (Absurdity)... ለመሳሰሉት) እንዲጋለጥ አስተዋፆ አድርጓል። ጥናቱበዚህ ፅንሰ ሐሳብ ላይ በማተኮር መገለጫዎቹን በተገቢው መንገድ የሚያሳዩ ታሪኮችን ከዚህ ፍልስፍና አንጻር የምፈትሽ ይሆናል። የኔና የአክሊሉን ጥናት የሚያገናቸው ይሄ ሲሆን ፣የሚለያቸው የእሱ ጥናት በአዳም አምስት መፅሐፍ ላይ በኤክስቴንሽናል ላይ መስራቱ ሲሆን የኔ ግን በአዳም የስንብት ቀለማት ረጅም ልቦለድ ላይ ጭብጥ መፈለግ ላይ ማተኮሩ ነው።

አክሊሉ በመጨረሻም የደረሰበትን እንዲህ አቅርቦታል፦

> "The first finding are that the narratives are existentialist stories and that Adam Reta is aliterary existentialist.The second is. . .that Adam has accomplished the concern of wellek and warren(1993) that ideas in literature should be "incorporated into the very texture of art. . .cease to be ideas in the ordinary sence of concepts and became symbols or even myths." As a philosophical thinking ,his idea have helped enormously to heighten the aesthetic value of his works .Finally, it can be listed on the same plane with Haddis Alemayoh,Bealu Girma,Dagnachew Worku,Tseg aye Gebremedhin.etc(35)

በአንደኛ ደረጃ አዳም ረታ ከሚያቀርባቸው ታሪኮች ተነስተን literary existentialist ነው ማለት እንችላለን ።በሁለተኛ ደረጃ  አዳም እነዌሌክና እነዋረን ጉዳዬ ብለው ያነሱትን የሥነፅሁፍ ውበት ጉዳይ እሱንም እንደሳበውና ነገሮችን ዝም ብሎ ማየት አቁሞ አፈታሪኮችን ሳይቀር ትእምርታዊ በማድረግ ማሳየት የቻለ መሆኑን ጠቅሷል።እንደፍልስፍና እሳቤ እሱ የሚያነሳቸዉ ሃሳቦች የሥነፅሁፉን ደረጃ ከፍ አድርጎታል።በዚህም አንጋፋ ከሆኑት የሥነፅሁፍ ሰዎች ከሀዲስ አለማየሁ፣ከበዓሉ ግርማ፣ከዳኛቸው ወርቁና ከፀጋዬ ገብረመድህን ተርታ ሊያሰልፈው ችሏል።

የአክሊሉ ጥናት ጠንካራ ጎን ጠጣሩን ጽንሰሐሳብ ባልተንዛዛ መንገድ ለጥናቱ እንዲስማማ አድርጎ ማስረዳት መቻሉና በምእራፍ አንድ ላይ ያቀረበውን አላማ በምእራፍ አራት  የመረጃ ትንተናውን ማሳየቱ ሲሆን፣ ለሁሉም ታሪኮች እኩል ትኩረት አለመስጠቱ (በዋናነት «ግራጫ

ቃጭሎች» ረጅም ልቦለድ ላይ  ብዙውን ጊዜ ማጥፋቱ) እንደ ድክመት ተስተውሏል፡፡ በዚህ ጥናት ይህን መሰሉን ክፍተት ለመቅረፍ ጥረት ይደረጋል፡፡

በሁለተኛነት በተዛማጅነት የተዳሰሰው ጥናታዊ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ በ1998 ዓ.ም በአበባው አቢ የቀረበው «የጭብጥ ትንተና በሙሽት ረጅም ልቦለድ» የሚለው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡ ጥናቱ በአራት ምዕራፎች ተከፍሎ የቀረበ ሲሆን የጥናታዊ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በ«ሙሽት» ረጀም ልቦለድ የጭብጥ ትንታና ማካሄድ ነው፡፡ «የአንድ የስነጽሑፍ ሥራ ጭብጥ ማለት የሥራው ማዕከላዊ ሐሳብ ወይም ጎልቶ የሚታየው ሐሳብ ማለት ነው፡፡» አበባው(1998፣ 4) አበባው የጭብጥ አወጣጥን በተመለከተ አራት ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ ጭብጦችን ወቅታዊና ሁለንተናዊ በማለት ከፋፍሏቸዋል፡፡  በዋናነት በእነዚህ ሁለት የጭብጥ አይነቶች መሰረት መረጃውን ተንትኗል፡፡ የአበባው ጥናት ጠንካራ ጎን ባስቀመጠው ጽንሰ ሐሳብ መሠረት በተገቢው መንገድ መረጃውን መተንተኑ ሲሆን ጥቅስ ወስዶ ምንጭ አለመጥቀሱ ደግሞ እንደ ጥናታዊ ጽሁፉ ደካማ ጎን ተስተውሏል፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ይህን መሰሉን ችግር ለመቅረፍ ጥረት ይደረጋል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ በተዛማጅነት የተዳሰሰው «በድህረ ፋሽስት ዓመታት በተጻፉ የአማርኛ ልብወለዶች ውስጥ ተደጋግመው የሚታዩ ጭብጦች» በሚል ርዕስ በ1976 ዓ.ም. በጌታቸው በለው የተዘጋጀው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍና ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ከ1933 እስከ 1953 ዓ.ም በታተሙ ልቦለዶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጌታቸው ለዚህ ጥናት እንደ አብይ አላማና አነሳሽ ምክንያት ያቀረበው ነጥብ አለ፡፡ «የሀገራችንን የፈጠራ ስነጽሑፍ ጉዞ ሂደት ለጥናት እንዲያመች አድርገን ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዋዜማ ጀምሮ በአራት ዘመናት መክፈል እንደሚቻል መገመት ይቻላል፡፡ ከ1890-1928 ዓ.ም.፣ ከ1933-1953 ዓ.ም.፣ ከ1953- 1966 ዓ.ም. እና ከ1966 እስከ 1976 ዓ.ም እያንዳንዱ ዘመን ለምን እንደዚህ እንደተከፈለ ራሱን የቻለ ታሪካዊ ምክንያቶችን መስጠት ይቻላል፣ ቢሆንም ግን ከዓላማ መዛነፍ እንዳይሆን ምክንያቶችን ከመዘርዘር እቆጠባለሁ፡፡ የስነጽሑፍ ጉዞ በዘመናት ተከፋፍሎ በቢጋር መልክ ይቀመጥ እንጂ በእያንዳንዱ ዘመን ላይ ግን አንዱን የስነጽሁፍ ዘርፍ በመውሰድ በወጉ የተጠኑ ስራዎች መኖራቸው ያጠራጥራል- ቢኖሩም የልብ አያደርሱም፡፡ እኔም ይህንን በመመልከት «ቅድሚያ ከራስ» በማለት ሁለተኛውን የስነጽሑፍ ዘመን፣ ከ1933-1953 ዓ.ም.፣ ያለውን ባጠናው ወደፊት ሰፊ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ እንደመነሻ የሚሆን ነገር ባበረከት ብዬ

ወሰንኩ።» ጌታቸው ከ1933 ዓ.ም. እስከ 1955 ዓ.ም ታትመው በወጡ ረጅም ልቦለዶች ተደጋግመው የተነሱ ጭብጦች– የኢጣልያ ወረራን አስከፊነት የሚያወሱ፣ ብሔራዊውን ኢትዮጵያዊ ጀግንነት የሚያሳዩ፣ የትምህርትን አስፈላጊነት የሚመሰክሩ፣ ባህላዊ ግጭትን የሚያንጸባርቁ፣ ፍቅርና ጋብቻ ላይ የተመረኮዙ፣ የዝሙት አዳሪነትን መራራ ሕይወት የሚያሳዩ፣ የመጠጥ ጎጅነት የሚመለከቱና ገንዘብ ለጥቅም መዋል አለበት ባይ ጭብጦች በሚሉ ስምንት አርዕስቶች ከፋፍሏቸዋል። በጌታቸው በእኔ ጥናት መካከል ያለው ልዩነት የጌታቸው ጥናት በአንድ የተወሰኑ ዘመን(ከ1933 ዓ.ም እስከ 1953 ዓ.ም) የተካሄደና በተጠቀሰው የጊዜ ክልል ታትመው በወጡ ረጃጅም ልቦለዶች ላይ የተካሄደ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በአንድ ወጥ ድርሰት ላይ የተካሄደ ነው። የጌታቸው ጥናታዊ ጽሑፍ ጠንካራ ጎን በ20 አመታት ውስጥ ታትመው የወጡ ረጃጅም ልቦለዶች በሙሉ መርምሮ በየልቦለዶቹ የተነሱ ጭብጦችን በተመጠነ ቋንቋ ማቅረቡ ሲሆን ስለጭብጥ መፈለጊያ ዘዴዎች በቂ ጽንሰሐሳባዊ ማብራሪያ አለመስጠቱ ደግሞ እንደደካማ ጎን ተስተውሏል።

በመጨረሻ የተቃኘው ጥናታዊ ጽሑፍ «የጭላንጭል ልቦለድ ታሪክ የጭብጥ ትንተና» በሚል ርዕስ በ1995 ዓ.ም. በተስፋዬ ንጉሴ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። ጥናታዊ ጽሑፉ በ1991 ዓ.ም. በታተመው በደራሲ ጌታቸው ደመቀ ረዥም ልብወለድ ላይ ነው። ደራሲው ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክት  ተንትኗል። አጥኚው እንደአነሳሽ ምክንያት ሁለት ነጥቦችን ያነሳ ሲሆን ደራሲው የዳሰሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች በሌሎች ደራሲያን ውስጥ በወጉ ያልተዳሰሱ በመሆናቸውና ድርሰቱ በጊዜው አሳሳቢ በሆነው በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ዙሪያ የሚያጠነጥን ስለሆነ ነው። በልብወለዱ ውስጥ እንደ አብይ ጭብጥ የተነሳው በማህበረሰባችን ስለኤች አይ ቪ ቫይረስና ቫይረሱ በደማቸው ስለሚገኝ ወገኖቻችን ያለውን የተሳሳተ አመለካከት ሲሆን ንዑሳን ጭብጦቹ ደግሞ ራስ ወዳድነት፣ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» እና ፍቅር ናቸው። ጭብጦቹንም ለመለየት አራት የጭብጥ መፈለጊያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል። የተስፋዬና የእኔ ጥናት በአንድ ወጥ ረጅም ልቦለድ ላይ ጭብጥ መፈለግ ላይ ያተኮረ መሆኑ ያመሳስለናል። ከዚህም በተጨማሪ የ«ጭላንጭል» እና «የስንብት ቀለማት» የጊዜ መቼት ተቀራራቢነት ያለው በመሆኑ በስንብት ቀለማት ውስጥ በኤች አይ ቪ ቫይረስ የተጠቁ ገጸባህሪያት አሉ። በትንተናው ውስጥ የሚነሳ ባይሆንም «በሩ ገርበብ ሲል» በሚለው ንዑስ ክፍል ውስጥ በቫይረሱ ስለተጠቃችና በማህበረሰቡ ስለተገለለች ገጸባህርይ የሚተርክ ክፍል አለ። በዚህም ክፍል ከ«ጭላንጭል» ልቦለድ ጋር ተመሳሳይነት አለው። የተስፋዬ ጥናት ጠንካራ ጎን በምዕራፍ ሁለት ማለትም በክለሳ ድርሳናት ስለጭብጥ ምንነትና ስለጭብጥ መፈለጊያ ዘዴዎች

ጥልቅ ጽንሰሐሳባዊ ቅኝት ማካሄዱና ቀደም ሲል ባስቀመጠው ጽንሰሐሳባዊ መመሪያ መሰረት የመረጃ ትንተናውን በተገቢው መንገድ ማካሄዱ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች አጥኚዎች ያላደረጉት አበይት ጭብጦችን ከለየ በኋላ በምን አይነት ዘዴ ጭብጦችን እንዳገኘ ጠቁሟል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የመረጃ ትንተና

### 3.1 የስንብት ቀለማት ረጅም ልቦለድ ዐብይ ጭብጥ

የአዳም ረታ የቅርብ ጊዜ ሥራ የሆነው የስንብት ቀለማት በ8 ምዕራፍ የተዋቀረ ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ በተለያየ ቀለማት ተሰይመዋል፡፡ ከዚህ ቀደም፣ እንደ ስንብት ቀለማት፣ ንቁ ተሳትፎ ያላቸው በርካታ ገጸባህሪያት የያዘ የአማርኛ ረጅም ልብወለድ አልታተመም፡፡ ልብወለዱ በፈረቃ በ"እኔ ባይ" እና በሁሉን አወቅ የትረካ አንጻር የቀረበ ሲሆን፣ ገፀባህርያቱ ትዝታቸውን፣ ደስታና ሀዘናቸውን፣ የከሸፈና የተሳካ የፍቅር ታሪካቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ የፖለቲካ ትግላቸውን፣ ጸጸታቸውን፣ ኑዛዜያቸውን.... በአጠቃላይ ነብስ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ አሁን እስከተጓዙበት እርቀት ድረስ ያሳለፉትን የሕይወት ውጣውረድ ይተርኩልናል፡፡ እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ታሪኮቹን እርስ በርሳቸው የሚያያይዙ ቀጫጭን ክሮች ቢኖሩትም ሁሉንም አበይት ገጸባህርያት ያካተተ የታሪኩን አጭር ቅርጽ (Short version of the story) በአንድ ወይም በሁለት ገጽ ማውጣት አስቸጋሪ ነው፡፡ ማውጣት ቢቻል እንኳ ሴራው ልል ስለሚሆን ተአማኒነት አይኖረውም፡፡

የስንብት ቀለማት ታሪኩ የሚጀምረው በ1987 ዓ.ም የክረምት ወራት በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደውን የመንገድ ማስፋት ሂደት በመተረክ ነው፡፡ የመንገድ ማስፋቱ ሂደትም ነባሩን የንፋስስልክ ቅርጽ በማፈራረስ፣ አሮጌውን በአዲስ በመተካት የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡
ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው ከጭብጥ መፈለጊያ ዘዴዎች ውስጥ የመጀመሪያው የልብወለዱን ርዕስ በጥንቃቄ ማጤን ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ዘዴ የልብወለዱን ጭብጥ ለማግኘት ሁልጊዜም ተመራጩ ዘዴ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ ሁልጊዜ ላይሰራ ይችላል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ የልብወለዱን አብይ ጭብጥ ተሸክሞ ሊገኝ ይችላል፡፡የዚህ ጥናት ጭብጥ የተገኘው ርእሱን በመመርመር ሲሆን ዐቢይጭብጡ ስንብት ወይም ሞት ነው፡፡

ሙሉጌታ የተባለ ተርጓሚና ሀያሲ የ"ስንብት ቀለማት በወጣበት ዘመንአንድ ሂሳዊ ፅሁፍአቅርቦነበር ፡፡በፅሁፋም ስለልብወለዱና ስለጭብጡ ጠቀም ያደረገው ነጥብ አለ፡፡

> The Colors of Adios (የስንብት ቀለማት) is the most recent novel by the famous contemporary Amharic writer Adam Reta.It is made of

eightchapters where each chapter is named after specific color.The titling of the chapters brings into attention victoria Finalys book color .A natural History of the palette'or Miles Davis'1989 album'Aura one might ask'what has the colors got todo with the stories?'The colors are more than Just titles.They were primerly used to design the morphology of the novel.The reader is asked to travel back in time to Newton &his experiments with light &prism.And also the colors are entwined with the content,as motifs,each color setting the theme of each chapter.(Mulugeta,2016,1)

በልብወለዱ ውስጥ ስምንት ምእራፎች እንዳሉ የሚገልፀው ሙሉጌታ እያንዳንዱ ምእራፍ ወይም ክፍል  በተለያዩ ቀለማት ተወክለዋል፤(ምእራፍ አንድ በነድ፣ሁለት በአረንጓዴ፣ሦስት በጥቁር፣አራት በሰማያዊ፣አምስት በቢጫ፣ስድስት በወርቅ፣ሰባት በቀይ፣ስምንት በነጭ)እንደሙሉጌታ አተያይ እኒህ ቀለማት ዝምብለውበዘፈቀደ የተወከሉ ሳይሆን በእያንዳንዱክፍል ለሚነሱ ጭብጦች ወይም ርዕሰ ጉዳዮች እንደ መንገሪያ ናቸው፡፡ይህም ጭብጡን በምናወጣበት ጊዜ ”ቀለማቱ ያላቸው ትርጓሜ ምንድነው ?”ብለን በመጠየቅ መነሳት እንችላለን፡፡ምእራፍ ሰባት በቀይ ተወክሏል፡፡ቀይ ቀለም ለጭብጡ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ምንድነው?ቀይ ቀለም ዘዉዲት በሻገር ሆቴል የደም ስሯን የተለተለችበትና እስከወዲያኛው ይህቺን ዓለም የተሰናበተችበት ክፍል ነው፡፡

". . .ሽራው ላይ ቀለም አፈሳለሁ፡፡ሰባትአይነትቀለማትአፈሳለሁ፡፡...ከዛምጭማሪቀለም አፈሳለሁ፡፡ብዙ ቀይ ይኖርበታል"(አዳም፣2008፣ 220)ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሰአሊው ወርቁ የቀለም አይነቶቹን በሙሉ ባይዘረዝርልንም በብዛት የሚጠቀመው ግን ቀይ ቀለም መሆኑን አውቀናል፡፡ይሄ ቀይ ቀለም ወዴት ይወስደናል ፡፡ወደ ዘውዲት ሞት፡፡ ንግር ነው፡፡ዘዉዲት የሰዓሊው ወርቁ ቀይ ቀለም የበዛበት ሸራ ላይ ከተንደባለለች በኂላ በሻገር ሆቴል ክፍል ቁጥር ሰባት ከናሆም ጋር ባሳለፈችበት አልጋ ላይ እንደአለም መድሃኒት እንደክርስቶስ ኢየሱስ እጆቿን መስቀለኛ ዘርግታ በደም በተነከረ አልጋ ላይ እስከወዲያኛው አሸልባለች፡፡የአለም መድሃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከሀጢአት ነፃ ለማውጣት ራሱን ቤዛ አደረገ ፡፡ዘውዲትስ ማንን ነፃ ልታወጣ ይሆን? የሷን ብጤ ወጣቶች ልታስተምር ይሆን?ዘውዲት የወደደችው ሰው ስለከዳት ተስፋ ቆርጣ (Despair) ወደዚህ ውሳኔ እንደገባች ከታሪኩ እንረዳለን፡፡

ዘዉዲት የወሰደችው እርምጃ ራሷን ብቻ የሚጎዳ ሳይሆን ቤተሰቦቿንም ነው::ቤተሰቦቿውስጥ ውስጣቸውን እድሜአቸውን ሙሉ የሚበላቸው ሀዘን ነው ::የልጅ ሞት ለዚያውም በዚህ አይነት ሁኔታ::የጎረቤት መጠቋቆሚያ መሆኑ የሚያሳድረው ስነልቦናዊ ጉዳትም ቀላል አይደለም::ይሄንን እንደ ኤክዝስቴሽናሊስቱ ሳርተር ገለፃ

> When I choose in the processe of making myself,I choose not only for myself but for all people.For instance,when a father is making a decision,he has to onsider his wife,children and his family as a Whole.He is totally responsile for any kind of consequence that may come upon him &the family.Put simply,freedom without responsiblity is dangerous &responsibility without freedom is hard to imagine.(stumpf,s&Fieser,200 3,78)

ከላይ ያየነው ጥቅስ አጠቃላይ መልእክቱ የምንወስነው ወይም የምንመርጠው ማንኛውም ነገር እኛን ብቻ የሚመለከት አይደለም በዙሪያችን ያሉትንም ጭምር እንጂ :: ነፃ መሆናችን ሀላፊነታችንን ካዘናጋን አደጋ አለው:: ለምንሰራው ስራ ሀላፊነት ይሰማን የሚል ነው::

ዘውዲትን ስናይ የራሷን ስሜት ብቻ አየችና ወደዚህ ውሳኔ መጣች ::ለቤተሰቦቿ የነበራትን ሀላፊነት ዘነጋች:: ይሄም ጉዳቱ ከፍተኛ ሆነ::

"ዘውዲት ዐልጋው መሀል ደም የተነከረ አንሶላና ብርድልብስ ላይ ራቁቷን ተኝታለች::(አዳም፣2008፣ 698) ለምን ራቁቷን?ደራሲው ይሄንን የመሰለ ወጣትነትን፤አፍላነትን ገፍታችኋል ፤ችላ ብላችኋል ሊለን ይመስላል:: ደበሌ በሚያነበው ጋዜጣ ላይ እንኳን ስለሚኒሊክ ሞት በቂ ትንታኔ ተሰጥቶት ሲፃፍ የዘውዲት አሟሟት ግን በአምስት መስመር እንደነገሩ ቀርቧል::የዘውዲትን አሟሟት ማንምጉዳዩ እንዳላለው ከጋዜጣው በተጨማሪ እዛው የሞተችበት ሆቴል ውስጥ እንኳን ወዲያው የተረሳ ይመስላል::"ከአንድ ሰዓት ተኩል በኋላ ግቢው በለመደው የቀድሞው ፀጥታ ተጠቀለለ"(አዳም፣2008፣ 701)ይህ ጥቅስ የዘውዲት ጉዳይ ተራ ነገር ነው ::ፖለቲከኛ ፣ታዋቂናሀብታም ብትሆን ግርግሩ ይበዛ ነበር::ዘውዲት ሃያ አመት ያልሞላት ባለትዳር ወዳ መከራዋን ያየች ወጣት ስትሆን በየስርቻው በተለያየ ሁኔታ እየተገፉ ላለፉ ፤ያለአግባብ ደማቸው ለፈሰሰ ወጣቶች ወኪል ነች::

ሌላው ያለምንም መረጃ በሜዳ ላይ ደሙ ፈሶ የቀረው የላስታ ልጅ ተስፋዬ ነው።"በስህተት ይሁን በብልጣ ብልጥ ብወዛ የእሱ ስም ተለጥፎበት ታድኖ በአብዮት ጠባቂዎች ስለተገደለው እዛ ቀይ ሜዳ ስለተጣለው ትክክለኛ ስሙ 'ተስፋዬ'ስለተባለው የንፋስስልክ ወጣት የሚናገር የለም"(አዳም፣2008፣ 424) ዓቢይ ጭብጡ ሞት መሆኑን በተለይም የነገ ሀገር ገንቢ ወጣት ያለበቂ ምክንያት እያለቀ መሆኑንያየንበት ነው።

ሌላው በዓብይ ጭብጥ ላይ የታየው የሻምበል ጉተማ ታሪክ ነው።ሻምበል ጉተማ በፍቼ ከተማ በበግ ንግድ የሚተዳደር ዘነቡ የምትባል ሴት አግብቶ ይኖር የነበረ ሰው ነው።ባለቤቱ ከእሱ በፊት ከነበራት ትዳር አንዲት ሴት ልጅ ነበረቻት።እርሱም ከእርሷ ጋር ለአራት አመታት ቢቆይም ልጅ ሊያገኝ አልቻለም ።በዚህም የመንደሩ ሰዎች በቀልድ በጨዋታ እያደረጉ አለመውለዱንሲያነሱበት ልቡ ሸፈተና በሚልሺያነት ተመልምሎ ወደ ውትድርናው አለም ተቀላቀለ።ከበግ ንግድ ያለምንም ስልጠና በቀጥታ ወደ ወታደርነትገባ።ሻምበል ጉተማ ከተራ ወታደርነት እስከ ሻምበልነት ለሀገሩ በሶማሊያው ጦርነት ተጋድሏል ።የአገሩን ዳር ድንበር አስጠብቋል በዚህም አካሉን አጉድሏል።በመጨረሻም ጀግኖች አምባ ሲኖር የደርግ ጦር ተበተነ ጀግኖች አምባም ተዘጋ ።ጎዳና ላይ ወጣ ።ለምኖ ለማደርም ተገደደ።

"እስከመቼ ልበሳጭ ፣ሲበርድልኝ፣ስቃጠል፣ስቀዘቅዝ ልኖር ነው?ልቤ ሃሞተቢስነቴን ይረግማል ።ምክንያቱም መሞትን እያሰብኩ ነበር።የሁልግዜ ስሜቴ ነው። ለምኖ ከመብላት ለምኖ ከመጠጣት ሕይወቴ ጋር በደም ስሮቼ ውስጥ የሚተላለፈው የመሞት ሀሳብ ነውና።"(አዳም፣2008፣645)ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አንድ ዋና ነገር ሻምበል ጉተማ በአካባቢው ሰው ሀሜትና ሽሙጥ ተገፍቶ በማያውቀው ሥፍራ ጎዳና መኖር እጣው ከሆነ ሰንብቷል።በመጨረሻምመሮታል።አንገሽግሾታል።የሚያስበውየሚያልመውመሞትንነው።እንደነገረ ህላዌ(existentialism)ገለፃ፦

> When I am dead, according to sartre.I lose the ability to look back,&thus my death makes me the future prey of living.This charge again depends on the existentialist assumption of an inner subjectivity that is isolated & alienated from others.(Drefus, 2006,p.286)

ሻምበል ጉተማ ጀግኖች አምባ ሲኖር ብርቱካን የምትባል ወዳጅ ነበረችው ።ጀግኖች አምባ ሲፈርስ ወደአገሯ እንሂድ ብትለው እምቢ አላት ምክንያቱም መውለድ አልችልም ብሎ ስላመነ አእምሮው አልተቀበለም። በመጨረሻ ግን ራሱን ለማጥፋት ሲወስን ከሳሪስ ተነስቶ በእግሩ

አባሳሙኤል ገባ ::ሬሳውን ማዘጋጃ እንዲቀብረውም አልፈለገም ::እዛ ጀግኖች አምባ ያወቃት ወዳጁ አባሳሙኤል ብርቱካን ሀገር ::"እንደማንም እዚህ እንደሚኖር መንገደኛ ሬሳዬ ረጂ ቆሻሻ ቦታ እንዲጣል አልፈልግም::ክርስቲያን ነኝ::ሃይማኖት አለኝ::ከሞትኩ ምኞቴ ብርቱካን ጋር ደጃፍዋ እንዲሆን ነው::"(አዳም፣2008፣645)ሻምበል ጉተማ መገፋቱ መገለሉ የፈጠረበት የብቸኝነት ስሜት ከልክ ያለፈ እንደነበር ከሚናገረው ንግግር እንረዳለን ::ከሞቀ ቤቱ ያወጣው አለመውለዱ እንደሆነ ይታወቃል :: ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ወደ አገሩ፤ ወደበግ ንግዱ ሊመለስ አይችልም እግሩን ተጎድቷል ::ባለቤቱ ዘነቡ እንድትጦረው አልፈለገም::ምክንያቱም ልጅ አልወለደላትም::ልጅ ቢኖር በልጁ ምክንያት ይመለስ ነበር::

በአቃቂ አቅጣጫ ብዙ ብንዝም በትክክል የት እንደ ደረስኩ አላውቅም::. . .ጥልቅ ብቸኝነት ተሰማኝ::ይሄ የመገለል ብቸኝነት ፣የመዘንጋት ብቸኝነት፣ያለመረዳት ብቸኝነት፣የደሃነት ብቸኝነት አልነበረም::የመጀመሪያው ብቸኝነት ይመስላል::. . .የብቸኝነቶች እናት::(አዳም ፣2008፣644) የሻምበል ጉተማ ባይታወርነቱ(alination) ጥግ ደርሶ የታየበት ገለፃ ነው::በጎዳና ተዳዳሪነቱም የዘድሬክ ካፌ ባለቤት አሸናፊ ሆቴሉ ላይ ቃጠሎ የደረሰበት እለት በደረሰበት ድብደባ የበለጠ ተጎሳቁሎ ነበረና ወደ አባሳሙኤል ወደ ብርቱካን ሀገር ጉዞውን አደረገ::የመጨረሻ ስንብቱን ለመፈፀም::

"ሞት ዳር ዳር እያልክ ሆዴን አታባባ!

አትቁም ከበሩ ሰተት ብለህ ግባ!"

(አዳም፣ 2008፣764) ከነዚህ መንቶ ግጥሞች ሻምበል ጉተማ ራሱን ለማጥፋት መወሰኑን ያየንበት ሲሆን ምናልባት ብርቱካንን ቀድሞ ቢያገኛት ኖሮ ለመሞት አይወስንም ነበር እንድንል ያደርገናል ::አንድም ለመወሰን ተቸግሮ እንደነበር እንረዳለን::መሞት ፈልጓል ግን ደግሞ ብርቱካንን ናፍቋል ::እንዲህ ሆኖ እንድታየው ደግሞ አልፈለገም::ግን እንደ ሰው ክብር አግኝቶ መቀበርም ፈልጓል::ይበርድሃልልብስህንለብሰህእንሂድስትለውነጪትእንኳን ልብሴን ምኔንም አልፈልገውምከዚህ ምልልስ የምንረዳው ሻምበል ጉተማ እራሱን የጠላበት ፤እራሱን ለማጥፋት የቆረጠበት እንደነበረ 'ምኔንም'ሲል ነፍሴን

የሚል እንድምታ አለው።ተስፋ መቁረጡ(despair) ራሱን ለማጥፋት እንዳደረሰው ያየንበት ክፍል ነው።

ልሂድ ካራ ቆሬ ብርቱካን መጋላ!

ለአንቺምለአገርአልሆንኩበውሃልበላ!አላህይቅርበለኝ፣ተክልዬ ማሩኝ!"(አዳም፣2008፣764)

ሻምበል ጉተማ ወደሞት እየተጓዘ ነው።'ለአንቺም ለሀገር አልሆንኩ'የሚለው ሐረግ መልእክቱ ጉዳቱ ከፍ ያለ ነው።አካላዊም አእምሮአዊም ነው።እኔ ሸክም ልሆንብሽ አልፈልግም ።ልጅ መውለድ አልችልም ።በዚህም የደረሰብኝ ስነልቦናዊ ጉዳት አለ ።ስለዚህ ለአንቺ አልጠቅምሽም።አሁን ለሀገሬም ማገልገል አልችልም ።ቀደም ብዬ ሀገሬን ከጠላት ስከላከል አካሌን አጉድያለሁ። ጎዶሎን የሚፈልግ የለም ።እንደ ሙሉ ሰው አልቆጠርም።አካሌን የገበርኩላት ሀገሬም ሜዳ ላይ እንደ ጉድፍ ጥላኛለች። ስለዚህ የኔ በዚህ ምድር ላይ መኖር ትርጉም የለውም የሚል ይመስላል።"Existential thinkers take man as the center of their philosophy &conted that the world is meaningless & absurd,so the individual is free &able to make sense out of its futile life."(Sarter,1946,p.6) ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው የነገረ ህላዌ(Existentialism) ዋነኛ ማጠንጠኛው የሰው ልጅ ሲሆን፣ሰው በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ምንም አይነት ፋይዳ ወይም ልኑርለት የሚለው የሕይወት ግብ እንደሌለውና ሕይወት ብዙዎቻችን እንደምናስበው አንዳች ተልእኮ ያላት ሳይሆን ከንቱና ትርጉም አልባ ናት።ስለዚህ ማንኛውም ሰው የራሱን እጣ ፈንታ በራሱ የመወሰን እንዲሁም በዚህ ትርጉም አልባ ዓለም ውስጥ የራሱን ትርጉም የመፈለግና ሕይወቱን እንዳሻው የመምራት ሙሉ ስልጣን አለው ብሎ ያምናል።

ከእነዚህ ከላይ ካየናቸው ድምዳሜዎች የምንረዳው ተመሳሳይ ነገር ምንድን ነው? የስንብት ቀለማት አብይ ጭብጥ፣ እያንዳንዱ ፍጥረት ሁሉም ወደሚፈራውና ወደማይቀርለት እርጅናና ሞት እየተንደረደረ መሆኑን (እንደ ምኒልክ ዓይነት እድለ ቢሶች ደግሞ ይህንን የሞት አገር ከአንድም ሁለቴ መጎብኘታቸውን)፣ ሁላችንም በየእያንዳንዱ ቅጽበት የልጅነታችንን ኬላ እያለፍን፣ እንደ ንፋስስልክ ትንንሽ ሱቆች፣ ቤቶችና ጎዳናዎች እየፈራረስን መሆኑን ማርዳት ነው።

## 3.2 የስንብት ቀለማት ረጅም ልቦለድ ንዑሳን ጭብጦች

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የስንብት ቀለማት አብይ ጭብጥ በመንፈስም በስጋም ግባችን መሰናበት መሆኑን ማርዳት ነው፡፡ ታድያ ይሄ በ940 ገጾች የተቀነበበ ረጅም ልብወለድ አንድ ነጠላ ጭብጥ ብቻ አለው ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ አብይ ጭብጥ ከውስጡ የሚመዘዙ ንዑሳን ጭብጦች ይኖሩታል፡፡ ጎልተው የታዩት የልብወለዱ ንዑሳን ጭብጦች፣ የ“ያ ትውልድ” ስህተቶች፣ የመበዳደል አዙሪትና ጭላንጭል ተስፋዎች በሚሉ ሦስት አርዕስቶች ተመድበዋል፡፡

### 3.2.1 የ “ያ ትውልድ” ስህተቶች

ወደ ትንተናው ከመግባቴ በፊት “ያ ትውልድ” ማነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ወርቁ የተባለው ገጸባህሪ “እኔ ‘ያ ትውልድ’ የምለው በ1966 በወጣትነት ጀምሮ እዚህ የደረሰውን ነው” (አዳም 280) ይላል፡፡

በድርሰቱ ዓለም ውስጥ የዚህ ትውልድ ዋነኛዎቹ ተወካዮች ምኒልክና ፊያሜታ ናቸው፡፡ ፊያሜታ “በእናቷ ሐማሴን በአባቷ ጎንደሬ፣ እኔስ እሆናለሁ እንደፍጥርጥሬ” ተብሎ የተገጠመላት ናት፡፡ ገጣሚው ምኒልክ ነው፡፡ የምኒልክ ወዳጆች እነ ዓለማየሁ ደግሞ “አስገንጣይ” በሚል ስም ይጠሯታል፡፡ በስልሳዎቹ መጨረሻ “ኤርትራ ስለተበደለች መገንጠል አለባት” ብለው ከተነሱ ወጣቶች መካከል አንዷ ናት፡፡ ምኒልክ ደግሞ እሷን የመሰሉ ወጣቶች አፍቅረው ሕይወታቸው እስከ እለተሞታቸው ምስቅልቅሉ ከወጣ እድለ ቢሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ጸጋ የተባለው ገጸባህሪ “We live in a totally political world...love do not have any place” (አዳም 325) እንዳለው የነፊያሜታና መሰሎቿ ልብ ለፍቅር ቦታ በሌለው የፖለቲካ ዓለም ውስጥ ቀልጦ የጠፋ ነበር፡፡ እንደ ምኒልክ ዓይነቶቹም ቢሆኑ ከፖለቲካ ውጭ መሆን የማይችሉበትና ገለልተኝነት “የሚያስመታበት” ዘመን ነበር፡፡ “It may be the devil or it maybe the lord, but you are gonna have to serve somebody” (አዳም 324) ለእግዚአብሔርም ሊሆን ይችላል ወይም ለዲያብሎስ ላንዱ ጌታ ማገልገል ግዴታ የሆነበት ዘመን ነበር፡፡ ፖለቲካ ውስጥ የለሁበትም ማለት እንደዛሬው ቀላል አልነበረም፡፡ ምኒልክና መሰሎቻቸው ፖለቲካ ውስጥ ምንም ዓይነት ዝንባሌ ባይኖራቸውም በዘመኑ አስገዳጅነት ምክንያት ወደ ፖለቲካዊ ዓለም ሊገቡ ችለዋል፡፡ ምኒልክ በልብወለዱ ውስጥ ያለው ንቁ ተሳትፎ እምብዛም ነው፡፡ ታሪኩ የሚጀምረው እሱ በሞት በተለየበት በ1987 ዓ.ም ሲሆን፣ ከመሞቱ በፊት ግን የራሱን ድምፅ በሁለት ካሴቶች ቀርጾ ለወጣቱ ገጣሚና ሰዓሊ ወርቁ ዕንቁ ባህርይ

ልኮለታል። ፍላጎቱም እንደ አርታኢ መደረግ የሚገባውን አድርጎ የሕይወት ታሪኩን በመጽሐፍ መልክ እንዲያወጣለት ነበር። ወርቁም የምኒልክን የህይወት ታሪክ ከሲዲ ወደ ወረቀት ገልብጦ "ጥቁር" በሚል ርዕስ አሳትሞለታል። ሳይወድ በግድ ፊያሜታን ለማስደሰት ሲል ብቻ ወደ ፖለቲካው ዓለም እንደገባ የሚነግረን ምኒልክ የልጅነቱን ጊዜያት መለስ ብሎ ሲቃኝ ስህተት እንደነበር ተረድቷል።

> ወታደር መቃወም ትክክለኛ የሆነ የተማሪ ባህል፣ ከእኔ የበለጠ የተማሩ ሰዎቹ የሚያውቁትና ያመኑበት እኔ ልረዳ ያልቻልኩት ዕውነትነት ያለውና ያለሁበት ትውልድ የመጨረሻው ቅዱስ ግብ ይመስለኝ ነበር። ምሁራኑ የታያቸው ነገር ከሌለ እዚህ ዓይነት ነገር ውስጥ ይገባሉ? እንዴት ያ ሁሉ ሰው ይሳሳታል?... በመፖትለኬ ቁምነገረኛ የሆንኩ መሰለኝ። (አዳም፣2008፣ 291)

በ1967 ዓ.ም የክረምት ወራት ዕድገት በህብረት ዘመቻ ፍቼ ከተማ ይዘምታል። ፍቼ ውስጥ ንጋት ከምትባል ልጅ ጋር ይተዋወቃል። እሱ እንደሚለው ንጋትን የቀረባት የእውነት ወዷት ሳይሆን "የአራዳ ምቾት ስለተነፈገና ለመዝናኛና ለጊዜ ማጥፊያ ነው።" (አዳም፣2008፣292) በመጨረሻም ስትጸንስበት ፍቼን ጥሎ አዲስ አበባ ይገባል። "አፍቃሪ ሳልሆን ሾተሌ ነበርኩ። የፍቼን ለግላጋ ቲሃ ነጥቄ፣ እንደ እርግብ ላባ የሚያደርገውን ቆዳዋን በቆሻሻ ቃንጤ አጠፋሁት።" (አዳም፣2008፣ 294) ምኒልክ ታሪኩን፣ ኑዛዜ ያለው፣ በፊያሜታ ቢበደልም እሱም ንጋትን መበደሉን ስለሚያውቅ ነው። አዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ ከፊያሜታ ጋር መታየቱንና ከአብዮት ጠባቂዎች ጋር ድብብቆሽ መጫወቱን አላቆመም። ምክንያቱም የፊያሜታ እውነተኛ አጀንዳ አልተገለጸለትም ነበር። ወይም ደግሞ እንደተሸወደ መቀበል አልፈልገም ነበር። በመጨረሻም በ1970 ዓመተምህረት አሸባሪ ተብሎ ይያዝና አራት ዓመት ይፈረድበታል። እስሩ የጎዳው እሱን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡን ጭምር ነበር። ለእሱ በጊዜው ትክክል መስሎት ተታሎ የከፈለው መስዋእትነት ከልጅነቱ ውስጥ አራት አመት ወስዶበታል። እናቱ እሱን ጥየቃ የእስር ቤት ደጆችን ደግመው ደጋግመው ረግጠዋል። አልቅሰዋል። አንብተዋል። ይሄ ሁሉ ግፍና በደል ሲደርስበት ፊያሜታ ጠይቃዋለች? በአገር ቤት ወግ እግዚአብሔር ያስፈታህ ብላዋለች? አፍቅሯት እንዲህ አይነት ጉድ ውስጥ ለገባ ወጣት ይሄ ልብ አይሰብርም? እሷ በዘመድ አዝማድና በገንዘብ ጉልበት ከሀገር ስትወጣ እሱ ግን አራት አመት ሙሉ በእስር ማቀቀ። እንደ ምኒልክ እምነት ከሆነ ለደረሰበት ሁሉ የፊያሜታ ብቻ ሳይሆን የእርሱም ጥፋት

ነበረበት፡፡ "ለመሆኑ ፊያሜታ ማን ናት? አላልኩም፡፡ በደደብ የልጅነት ትዝታ ተነድቼ በቀንበሯ በሬኛ ገባሁላት፡፡" (አዳም፣2008፣335) ይላል፡፡ ታሪኩ የምኒልክና የፊያሜታ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ መሰሉ ታሪክ የዚያ ዘመን ወጣቶች የፍቅር ታሪክ ነው፡፡

የምኒልክን ድምጽ ወደ ወረቀት በመገልበጥ፣ በመጽሐፍ መልክ የሕይወት ታሪኩን አትሞ ያወጣው፣ ሰዓሊውና ገጣሚው ወርቁ የሚኒሊክን ሕይወት 'ስህተት ነበር' ይላል፡፡ ስህተትነቱም አመለካከቱ (በዋናነት የነበረው ፖለቲካዊ ዝንባሌ ) ከራሱ ጭንቅላት የፈለቀ አለመሆኑ ነው፡፡ የታገለው በሌሎች ሰዎች፣ በዋናነት በፊያሜታ እና በመሰሎቿ ተታሎ ነው፡፡ ኤርትራውያን በተለየ እንደተበደሉና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚያስተሳስራቸው ምንም አይነት ታሪካዊ መሠረት እንደሌለ ወሬ ማሰራጨት አንደኛው የነ ፊያሜታ ፖለቲካዊ 'ታክቲክ' ነበር፡፡ ይህ አይነቱ ወሬ መሠረተ ቢስ መሆኑ ቢታወቅም ሲደጋገም ግን እውነት መስሎ መታየቱ አይቀሬ ነው፡፡ ምኒልክ በ1974 ዓመተምህረት ከእስር ከተፈታ በኋላ፣ ሳፍሮን የተባለች ሴት በትዳር አግብቶ ሦስት ሴት ልጆች አፍርቶ ይኖር ነበር፡፡ በትዳሩ ደስተኛ ነበር? ፊያሜታን በወደደበት መጠን ዙፋንን ይወዳታል? እድሜውን በሙሉ ያሳለፈው ስለ ፊያሜታ ሲያወጣና ሲያወርድ ነው፡፡ ከልቡ ስለነበረ የወደዳት ከትውስታው ሰሌዳ ሊፍቃት አልቻለም ነበር፡፡ ከሀያ አምስት አመት በኋላ የኢህአዴግ ካድሬ ሆና ከአሜሪካ አዲስአበባ ስትመጣ ሊያገኛት ጓጉቶ የነበረውም ለዚህ ነበር፡፡ ግን ነገሮች ባሰበው መንገድ አልሄዱለትም፡፡ 'ምኒልክ ነኝ' ብሎ ሲተዋወቃት 'ይቅርታ አላስታወስኩህም' ነበረ መልሷ፡፡ ይህ ክስተት ምኒልክን እስከወዲያኛው የሰበረ ነበረ፡፡ በአፍላነቱ ለወደዳት፣ ደርጉን 'ፋሺስት' ብሎ ለሰደበላት፣ አራት አመት ከርቼሌ ለወረደላት፣ ሲታሰር ባትጠይቀውም እንኳ ይቅር ላላት፣ ልጅነቱን መሰዋዕት ላደረገላት..... ምላሿ 'አላስታወስኩህም' መሆኑ ልቡን ሰብሮታል፡፡ ልቧ ውስጥ እንኳ ባታስቀምጠኝ ትዝታዋ ውስጥ የለሁም? ብሎ ማሰቡ አልቀረም፡፡ ይሄም የፊያሜታ ምላሽ ብቻውን እስከማውራት ዳርጎታል፡፡ ጉዳዩን ቼቼ እንዲህ በማለት ትገልጸዋለች፡፡ "አንዳንድ የሸወዳ ጥበብ አሪፍ ከመሆኑ የተነሳ ተሸዋጁንም አልተሸወድኩም እንዲል ያደርገዋል... አንዳንዱ ሰው እራሱንም ይሸውዳል፡፡" (አዳም፣2008፣388) ምኒልክ በፊያሜታ የደረሰበትን ሽንፈት ላለመቀበል ሲያደርገው የነበረው ጥረት እጅግ አሳዛኝ ነበር፡፡ "አንዳንድ የሸወዳ ጥበብ አሪፍ ከመሆኑ የተነሳ ተሸዋጁንም አልተሸወድኩም እንዲል ያደርገዋል" ትግል ሕይወቱን ሲገልጽም፡፡"ምናልባት በትክክል ምን እንደሚፈልግ፣የሚፈልገውንም ነገር በምን አይነት መንገድ እንደሚያገኝ ያልገባው ትውልድ ውስጥ ነበርኩ፡፡"(አዳም፣2008፣ 305) ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ነገር ምንድነው?ምኒልክ ምን እንደሚፈልግ ያወቀ ነገር ግን የሚፈልገውን ነገር በምን አይነት መንገድ እንደሚያገኝ ያልገባው

ትውልድ ውስጥ ነበረ። ፊያሜታን እንደሚወዳት ያውቃል። ፍቅሯን ይፈልገዋል። ይሁንታዋን ግን በምን አይነት መንገድ ማግኘት እንዳለበት አላወቀም ነበር። ሀሳቤ እንዳንቺ ነው እያለ እሷን ለማስደሰት ብዙ ጥሯል። ይህ ነገር ምኒልክን ብቻ የሚመለከት አይደለም። ፊያሜታንና ቤላንም ይጨምራል። በእርግጥ ምኒልክ ደርግን የጠላው የእውነት ደርግን ጠልቶ ነው ወይስ በፊያሜታ ተታሎ?"ቆላጥነት ምንድንነው?-ያው የፈለገው መጣለታ እለዋለሁ።-ለዚህ አይደለም የታገለው ይለኛል።(አዳም፣2008፣361) ከዚህ የቹቹና የምኒልክ ምልልስ ውስጥ አንድ የምንረዳው ነገር አለ።ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ምኒልክ ምን እንደሚፈልግ ከማያውቁት የዚያ ትውልድ አባላት መካከል አንዱ ነበር። ደርግን የታገለው ደርግን ጥሎ የፊያሜታን ወገኖች ዙፋን ላይ ለማስቀመጥ ነበር (አቋሙ ከራሱ ጭንቅላት የፈለቀ ባይሆንም እንኳ የታገለው ለዚህ ዓላማ ነበር።) ሕወሃት ወደ ስልጣን ሲመጣ ግን ደስተኛ አልነበረም። ምክንያቱም እሱ የታገለው ለፊያሜታ ፍቅር እንጂ ለሕወሃት አልነበረም። 'ለዚህ አይደለም የታገለው'የሚለው እንደዘበት የተወረወረ ዓረፍተነገር፣ ለዚህ አልነበረም የታገልኩት የሚል አንድምታ አለው።

ቤላ/ መአዛ/ በ1966ቱ አብዮት ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ ነበራት። ደርግን ትቃወም፣ ለኤርትራ ትሰልል የነበረው ግን ለኤርትራውያን ወገኖቿ ተቆርቁራ ወይም የትግሉ ስር መሰረት ገብቷት አልነበረም- በአሳዳጊዋና በማህበረሰቡ ምክንያት የደረሰባትን  በደል ለመሸፋፈን እንጂ።"መልከ ጥፉን በፖለቲካ ይደግፉ ሲባል አዳሜ ላትሰሚ ትችያለሽ።ግን ይባላል።በኋላ የ66አብዮት ተነስቶ ተሳተፊ ብለው ሲመለምሉኝ በፖለቲካው ውስጥ ፋንጋነቴ ጠፋ።(አዳም፣2008፣85)ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው የቤላና መሰሎቿ የፖለቲካ ትግል"ሞቲቭ"ተጨባጭ ምክንያት አልነበረውም። ከዚያ ይልቅ ግላዊነቱ ያደላል። ገፀባህርያቱ ወደ ትግል ህይወት የሚገቡት ከራሳቸው ግላዊ ጣጣ ለማምለጥ አልያም ደግሞ 'አቻ ግፊት፣ የአገር ልጅነት፣ ጓደኝነት፣ ገርል ፍሬንድነት' በመሳሰለው ተታለው ነው። ቤላ ወደ  ፖለቲካው ዓለም የገባችው *ጭቁኑን የኤርትራ ህዝብ* ነጻ ለማውጣት ሳይሆን ራሷን ከማህበረሰቡ ስድብና ወቀሳ ለማራቅ ነው።

ፊያሜታም ልክ እንደ ምኒልክ የከሸፈው ትውልድ አባል ናት። አመለካከቷ እንዳለ ሆኖ (*ለኤርትራ ነጻነት መታገል አልነበረባትም ማለት ስለማንችል*) ከተሳሳተው ትውልድ ዝርዝር ውጪ ልትሆን አትችልም። ቤተሰቦቿ ተታለው አታልለዋታል። “የኤርትራ ሰዎች በሙሉ አሪፍ፣ ኢትዮጵያውያን ግን ደደብ እንደሆኑ፤ በመስሪያ ቤታቸው ከማንም ተመርጠው ከባድ ሀላፊነት እንደተሰጣቸው፣ አገሪቷን በማሰልጠን ላይ እንዳሉ(እንደፈረደባቸው) አድርገው ነው

አባቷ የሚያወሩት።" (አዳም 485) ከሚለው የቤላ /መዓዛ/ ቃላቶች ጋር እያንሰላሰልን ስናነበው የሚሰጠን አንዳች ትርጉም አለ። አስገንጣዮቹ ዓላማቸውን ለማሳካት ሲሉ በመካከላችን መቃቃርን የሚያሰፍኑ ነገሮችን ፈጽመዋል። "በወንድምነት፣ በጓደኝነት፣ በአብሮ አደግነትና በገርል ፍሬንድነትና በጨቋኝነት በመሳሰለ" ዘዴ ነጣጥለውናል።"የዕውቀት መጀመሪያ መጠራጠር መሰለኝ።መብሰል የሚጀምረው እውነት ተብሎ የሚሰጠኝን (በወንድምነት፣በጓደኝነት፣በአብሮ አደግነት፣በገርልፍሬንድነትናበጨቋኝነት በመሳሰለ) ተሸፋፍኖ የሚመመጣውን መረጃ በጥያቄ መፈታተን ነው።"(አዳም፣2008 ፣239)የተነገረንን ሁሉ እንደወረደ ከማመንና ከመተግበር በፊት የተነገረንን ነገርና የነጋሪያችንን ዓላማ (intention) ማጤን ይገባል። መረጃን መርምሮ መውሰድ ብስለት ነው። ያ ትውልድ በዚህ ረገድ ብዙ ቀርነቶች ነበሩበት። ከእውነታ ይልቅ ለጓደኝነትና ለአገር ልጅነት ቦታ ይሰጥ ነበር።

ፊያሜታና መሰሎቿ የታገሉትና እድሜያቸውን የጨረሱት ባልተረጋገጠ ነገር ላይ ነው። "ተበድለናል!" የሚሉት ከበላዮቻቸው የሰሙትን ይዘው ነው። ከኤርትራ ወጥቶ የማያውቅ ሰው ይህን ቢል ተቃውሞ ሊገጥመው አይችልም። ምክንያቱም ኤርትራዊ እንዳልተበደለ መናገር አንችልም። መሃል አገር ተወልዶ ያደገ ግን ይህን ቢል (ያውም መሃል አዲስአባ ንፋስስልክ) ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም እኔ በተለየ ተበድያለሁ ካለ እየዋሸ ነው። ከተበደለም ባገር የመጣ ነው። ዓለማየሁ የተባለው ጓደኛው እንዲህ ይላል።"ፊያሜታ ከኛ ጋር ብዙ ብዙ አሳልፋለች አይደል።አልበደልካትም።ግን ያን የሚያምር የግል ትዝታዋን አጉድፋዋለች።"(አዳም፣2008፣ 322)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ምንድን ነው? ምኒልክም ሆነ ፊያሜታ ተበለጥኩ/ተታለልኩ ብለው የመናገር ድፍረቱ ካልነበራቸው ሰዎች መካከል ናቸው። ፊያሜታና ወገኖቿ ራሳቸውን እንደ ስልጡን የመሃል ሀገሩን ሰው ደግሞ እንደ ኋላ ቀር ቢያዩትም ቅሉ እነሱም ቢሆን ከመሃል ሀገሩ ሰው የተለዩ አልነበሩም።

የስንብት ቀለማት ታሪክ የባዕዳንን ተልዕኮ ባነገቡ የኤርትራ የነጻነት ታጋዮች የበላይነት የተዋቀረ ነው። የበላይነቱ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ንቃተ ሕሊናዊ...በመሳሰለው ሁሉ ነው። ሂራክሊተስ የተባለው ገጸባህሪ "ቀኝ ገዥዎች ቢዘገዩ የረሱህ እንዳይመስልህ።" (አዳም ፣2008፣242) ይላል። ቀኝ አገዛዙ ቅርጹን ለውጦ ቢሆንስ? ሀገር ወዳዱና አፍቃሪው እንደቂል ተቆጥሯል። ወርቁ ሮማንን ተነጥቋል። ነጣቂው ፀሐይ ነው። (በእርግጥ ፀሐይ ሮማንን ፈልጓት ነው?.....ወይስ እሷ ነው የፈለገችው?) አሸናፊ የትዕግስትን ሻገር ሬስቶራንት

በከፊልም ቢሆን አስፈርሷል፤ ይሄ ምጣኔ ሀብታዊ ብልጫ ነው፡፡ ሙሴ ደበሌን አሳስሯል፡፡ ይሄ ደግሞ ፖለቲካዊ የበላይነት ነው፡፡ ፊያሜታና ቤላ አፍቃሪዎቻቸው ላይ እስከ እድሜያቸው ጭላጭ ቀልደዋል፡፡ይሄ ንቃተ ሕሊናዊ የበላይነት ነው፡፡

ከዚያ ትውልድ መዝሙሮች ውስጥ አንዱ ወጣት ድሮ ቀረ ነው፡፡ ይህም ራስ ወዳድነታቸው ነው፡፡ ዮሐንስ ወላይሶ የተባሉት የዚያ ትውልድ አባል ስለትውልዳቸው ሲናገሩ ሰባት ህመሞች ነበሩበት ይላሉ፡፡"ሁሉም ያለምሕረት ያለበቂ ትንታኔ የዛሬውን ወጣት ያማሉ ፡፡እነዚህን እድለቢስ ጠማማነትን የተረከቡትን ጉብሎች ሲከላከሏቸው የምናየው ጥቂቶች ናቸው፡፡ወጣት ድሮ ቀረ አንዱ ወሬአቸው ነው፡፡ድሮ ሲሉ 'እኛ' ማለታችን ነው፡፡. . .ይኼም ስድስተኛው ሕመም ነው፡፡"( አዳም፣2008፣430) የትውልድ ንቃተ ሕሊና በሀገሪቱ ምጣኔ ሀብታዊ አቅምና በምትዘረጋው የትምህርት ሥርዓት ጥራት ተጽዕኖ ሥር የወደቀ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ትውልድን ለይቶ መውቀስ አግባብነት የለውም፡፡ ምኒልክና መሰሎቹ ወጣት ድሮ ቀረ ሲሉ እኛ ማለታቸው ነው፡፡ ይሄ አይነቱ ፍረጃ ደግሞ ምንም አይነት ማስረጃ የማይቀርብበት ከመሆኑ በላይ ከራስ ወዳድነት የሚመነጭ 'ኢጎ ሴንተሪክ' ሀሳብ ነው፡፡ የሚጠቀሙበትም የታናናሾቹን ሞራል ለመስበርና ራሳቸውን ከፍ ከፍ ለማድረግ ነው፡፡ ዮሐንስ ወላይሶ ይሄንን እንደ ትውልዱ በሽታ ይቆጥሩታል፡፡

የምኒልክ የግል ጉዳዩ ፊያሜታ ነበረች፡፡ ለሰው ለመንገር ግን ድፍረቱ አልነበረውም፡፡ ዮሐንስ ወላይሶ የዚያ ትውልድ አባል ቢሆኑም የትውልዱን በሽታ አልሸሸጉም፡፡ በዚህም ነቀፋና የስድብ ውርጅብኝ ደርሶባቸዋል፡፡ ትውልዱ ራስ ወዳድ ነበር ሲሉ እኩዮቻቸው ጥርስ ነክሰውባቸዋል፡፡ ለዚህም ይመስላል ይህንን ያሰፈሩት፦"በተለያየ ጥበብ ራሱን ሊያድን የሚሯሯጥ አለ፡፡ እኔ አልሯሯጥም፡፡ ራስ ወዳድነቴን ሁሉ ሰው እንዲያየው አደርጋለሁ . . . How foolish I am."(አዳም፣2008፣430) ምኒሊክ ሕመማቸውን ከደበቁ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ለሞት የዳረገውም ይህው ነው፡፡ ሕመሙን መደበቁ፡፡ እንደተሳሳተ አለማመኑ፡፡ ፊያሜታ ስህተቱ እንደነበረች ቢያምን ኑሮ እስከ እድሜው ፍጻሜ ድረስ ባልወደዳት ነበር፡፡ ለባለቤቱ ሳፍሮን (ዙፋን) እና ለልጆቹ ለእነ ቤርሳቤህ ተገቢውን ፍቅር መስጠት ያልቻለውም በፊያሜታ ወጥመድ ውስጥ ወድቆ ስለነበረ ነው፡፡ How foolish I am, (ምንኛ ቂል ኖሪያለሁ?) የሚለው የኑዛዜ ስንኝ የሚኒሊክን ሕይወት ጠቅለል አድርጎ የሚገልጽ ይመስለኛል፡፡"አንዳንድሰዎችያጋጥሙኛልያለፈውንመንግስትደልግማለቴነውማድነቅይወዳሉ፡፡አይገ ልምም?ሲጀመል ማን ተቃወሙት አላቸው ? አሁን በዛ በተሳደቡበት አፋቸው መንግስቱ ...እኮ ለችግለኛ ያስባል ምናምን ለአገል ያስብ ነበል ምናምን ይላሉ. . .የምን ማሽቃበጥ

ነው?(አዳም፣2008፣363) ይህ አይነቱ የፍላጎት መዛነቅ የተፈጠረው ከመጀመሪያው ምን እንደሚፈልጉ ሳያውቁ ስለ ታገሉ ነው፡፡ የታገሉለት ዓላማ ቢገባቸው ኖሮ ለውጡ ሲመጣ ደስተኛ ይሆኑ ነበር፡፡ ይህም ከዚያ ትውልድ ስህተቶች ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ የታገሉለትን ዓላማ በትክክል አለማወቅ፡፡ ምኒልክና መሰሎቹ የተጓዙበትን የሕይወት ጎዳና ቃል በቃል "ስህተት ነበር፣ ተሳስቻለሁ" ብለው ከማመን ይልቅ በሌሎች ሰዎች ማሳበብን መርጠዋል፡፡ ምኒሊክ በግለ ታሪኩ ስለ ትግል ሕይወቱ ስህተትነት ሳይሆን ሲያብራራ የነበረው፣ ስለ ፊያሜታና መሰሎቿ ተንኮልና ሴራ ነበር፡፡ ይሄ ደግሞ የያ ትውልድ ሌላኛው ህመም ነው፡፡

## 3.2.2 የመበዳደል አዙሪት

ሕይወት ውስጥ መበዳደል እና መመቀኛኘት ያለ ነገር ነው፡፡ የስንብት ቀለማት ውስጥ ያለው መበዳደል ግን ሥጋ ለብሶ የሚታይ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ብሔርተኛውን አስገንጣዮች ሲጫወቱበት እንመለከታለን፤ ተፈቃሪ አፍቃሪን ይበድላል (ምኒልክ እና ፊያሜታ፣ ወርቁ እና ሮማን፣ ቤላ እና ጅግሳ፣ ዘውዲት እና ናሆም ወደ አእምሯችን ይመጣሉ)፣ ወታደሩን ወታደር ያብጠለጥለዋል (እዚህ ላይ ለለይኩን ከንፈር እንመጣለን)፣ ባለትዳሯን ላጤዋ ጓደኛዋ ትመቀኛታለች (እዚህ ላይ ደግሞ ሳላይሽን ያስታውሷል)፣ ከያኒውን ሀያሲው ይዘልፈዋል (ፀሐይና መሰሎቹን ይጠቅሷል)፣ ሀገር ወዳዱን አስገንጣዮች ያስሩታል (ደበሌን ያስታውሷል)፣ አቶ ጉርሙን ህብረተሰቡ (ልጅ መውለድ ስላልቻለ)፣ ምትክን እነ አሸናፊ (መልክ ጥፉ ስለሆነች)፣ አቶ ዮሐንስን እነ ፀሐይና መሰሎቹ (ወጣቶቹን ከያኒያን በብዕር ጋሻቸው ስለተከላከሉ)… ጠቅለል ሲል ሆን ብለው ገፀባሕርያት ገፀባሕርያትን ሲበድሉ እንመለከታለን፡፡ ስለመበዳደል ስናወራ በዳይና ተበዳይ እንዳለ ግልጽ ነው፡፡ የስንብት ቀለማት ውስጥ ግን በዳዩንና ተበዳዩን መለየት አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱም በዳዩም ሌላ በዳይ አለበት፡፡ ያኛውም በዳይ ሌላ በዳይ አለበት፡፡… ('ለሀይለኛም ሀያል ለአጥቂም አጥቂ አለበት፣ አሰንብተኝ አምላክ ባይኔ ጉድ ልይበት እንዲል ስነቃላችን፡፡')

የዚህ ጥናት ትኩረት በልቦለዱ ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸው ገጸባህርያት እንደመሆናቸው መጠን የተወሰኑትን የመበዳደል ታሪኮች እናነሳለን፡፡

የስንብት ቀለማት ገጸባህሪያት ከስልሳዎቹ መጀመሪያ እስከ ሰማንያዎቹ መጨረሻ በተዘረጋው የጊዜ መስመር ላይ ያለፉ እንደመሆናቸው፣ ሀገሪቱ፣ ታላላቅ ለውጦችን ስታስተናግድ ለመታዘብ ችለዋል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የለውጡ አካል ነበሩ፡፡ ታድያ በሥርዐቱና በዘመኑ

አስገዳጅነትም ሆነ ባላቸው ግላዊ ዝንባሌ አማካይነት ገፀባሕርያት ሲበዳደሉ፤ ሲመቀኛኙ እና ሲወቃቀሱ እንመለከታለን።

የስንብት ቀለማት ገጸባህርያት አንዳንዴ በቀጥታ ተሳታፊነት አንዳንዴ ደግሞ በሐሜት፣ ስም በማጥፋትና በመሳሰለው ስልት ባላንጋራዎቻቸውን ሲበድሉ ይስተዋላል። እርስበርስ መመቀኛኘት ዋነኛው የግጭቱ መገለጫ ይመስለኛል። ምቀኝነትና ጥላቻ ጎልተው የሚታዩት የገፀባህሪያቶቹ ጠባያት ናቸው። ከአዲስአባ ሸሽቶ ወደ ሱልልታ የተሰደደው ሳምራዊው የተባለው ውሻ ስለ አዲስአባ ነዋሪዎች (በተዘዋዋሪ ስለልቦለዱ ገጸባህርያት ማለታችን ነው) የሚከተለውን ብሏል፦

"ከአዲስአበባ የመጣሁት እኮ አዲስአበባን ልሸሽ ብቻ አይደለም ከተማ የሚባል ሸሸቼ ነው።ጨካኝ ነው ከተማ።...ውሻውን ተወው ሰው አይማማርም። ምቀኝነት ዐእንደከብት ዐይነምድር በየቦታው ወድቆ ታያለህ።" (አዳም ፣2008፣402) ይህን የሚለው ሳምራዊው የተባለው ውሻ  ነው።ደራሲው ረቂቁን ምቀኝነት ከግኡዙ ዐይነምድር ጋር በተነፃፃሪ ዘይቤ በማነፃፀር በከተማችን ያለዉን ስር የሰደደ መመቀኛኘት አጉልቶ አሳይቶናል። ሳምራዊው አዳም ከበኩር የአጫጭር ልብወለድ መድበሉ “ማህሌት” ስቦ ያመጣው “ገፀባህርይ” ነው። የአዳም ረታ ልብወለዶች ውስጥ እንሰሳት ሁሉ እንደ ሰው ልጆች የራሳቸው ዓለም አላቸው። እንደ ሰው ያወራሉ፣ ይጫወታሉ፣ ይዋቀሳሉ። ሳምራዊው ለረጅም ዓመታት አዲስ አበባ ውስጥ ኖራል። በመጨረሻ ግን አዲስ አበባ ውስጥ ኖሮ ስላልተስማማው ወደ ፍቼ ተሰዷል። ፍቼ በሄደበትም አልደላውም። ቁርስ ምሳ ራቱ ሳር ነው። ግን ከአዲስ አበባ እንደሚሻለው ደጋግሞ ይናገራል። ይሄን ለማለት ያበቃውም የሰው ልጆች ጠባይ መክፋት ነው።

ሳላይሽ የተባለችው ገፀባህሪ ደግሞ እንዲህ ትላለች፦"ምናለበት ግን ብቀና?ይህቺ ሀገር እኮ የምትነቃነቀው በምቀኝነት ፎርሳ ነው። ከመሬታችን ባንችልበትም ልቦናችንን ቆፍረን ያወጣነው ነዳጅ ይሄ ነው።"(አዳም፣2008፣172) እንደሀገር ምቀኝነት ትልቁ ሳንካ ነው። እርስበርስ መተሳሰብና መዋደድ ሲገባን እንነቋቆራለን።መተጋገዝ ሲገባን  እንወቃቀሳለን። ልባችን በሙሉ በጥላቻ ተሞልቷል። አሉባልታ፣ ሸሙጥ፣ ሐሜት፣... መለያ ባሕርያቶቻችን ናቸው። “ከመሬታችን ባንችልበትም ልቦናችንን ቆፍረን ያወጣነው ነዳጅ ይሄ ነው” የሚለው ዓረፍተ ነገር መሬታችን የሚሰራበት አጥቶ ጦሙን ውሎ አድሯል ሰባራ ሰላላ ምክንያት እየደረደርን እጃችንን ከስራ እንዳራቅነው ፤በተቃራኒው ግን አእምሮአችንን በክፋትና በተንኮል እንደሞላነው

ያረዳናል። በአሉባልታ፣ ሽሙጥ፣ ሐሜትና በመሳሰለው ዘዴ ከተበደሉ ገፀባህርያት ውስጥ ግንባር ቀደሞቹ የንጋት እንጀራ አባት ሻምበል ጉተማ እና የሳላይሽ ወዳጅ ሻምበል ለይኩን ይጠቀሳሉ። አቶ ጉተማ ፍቼ ከተማ ከሚወዳት ባለቤቱ ጋር ለረጅም ጊዜ ሲኖር ልጅ ባለመውለዱ ምክንያት ሐሜትና አሉባልታ ይደርስበት ነበር።

"የመሀንነት ድክመቴን በጨዋታ መሀል እያነሱ በነገር የሚወጉኝ የሚያሽሟጥጡኝ አልጠፉም። የሰዎቹ ተረብ ጨዋታ ነው ቢባልም፣ጨዋታ ቢሆንም፣ውስጤ ድረስ ሀዘን ያምሰኛል። የምተዳደርበት የበግ ንግድ ወንድነትን ይሁን የሀገር ወዳድነትን የሚለካ አልነበረም።"(አዳም ፣ 631)ዚያድ ባሬን ሊዋጋ የዘመተውም በዚህ የተነሳ ነው። ከማህበረሰቡ ያጣውን ፍቅርና ክብር ለማግኘት። ሀገሩን ከወራሪ ጠላት ለመከላከል። የሀገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር። ወንድነቱን ለማሳየት። በጦርነቱ አንድ እግሩን አጥቷል። የሚገባውን ክብር ግን አላገኘም። አዲሱ ሀይል አሸንፎ ሠራዊቱ ሲበተን ጎዳና ተዳዳሪ ለመሆን ተገዷል። “ወሰናቸውን ስጠብቅላቸው አካሌን ባጎድልም፣ ከምንም የማይቆጥሩኝ መዓት ናቸው።” (አዳም፣2008፣635) እዚህ ላይ በዳይና ተበዳይ ማን ነው? ሻምበል ጉተማ ሚስቱን ጥሎ የዘመተው፣ እግሩን የገበረው ሲያሽሙዋጥጠው የኖረውን ሕዝብ ከወራሪ ጠላት ለመከላከል ነው። “አገሬን ነክተውብኝ ጮኼ የተነሳሁ ነኝ። ምርምር አላደረኩም። ተማርን እንደሚሉት አገሬን በቃላት ነዝንዤ በፉክክርና ምቀኝነት ለጠላት አልሰጠሁም” (አዳም ፣2008፣635) እግሩን ካጣ በኋላ ግን ወደዚያ ማህበረሰብ ለመመለስ ወኔ አልነበረውም። አዲስአበባ ጎዳና ላይ መሞትን መርጧል። ከማህበረሰቡ ሽሙጥ ይልቅ የአዲስአባን ቁርና ሀሩር መርጧል። ይህም ሕዝብ ግለሰብ ላይ እንደፈጸመው ሀጥያት ይቆጠራል። ይህን እንድል የገፋፋኝ ይህ ዓይነቱ ክስተት ሁለት ሦስት ገፀባህርያት ላይ በመፈጸሙ ነው። ሻምበል ጉተማ ስለ ወትድርና ሕይወቱ ሲተርክ፣ ተመሳሳይ ችግር ስለነበረበት ለይኩን ስለተባለ ጓዱ ያጫውተናል።

ይህን ዓይነቱን ከሐረርጌ ሱሉልታ፣ ከሀገር ጫፍ እስከ ጫፍ የተዘረጋ የሐሜትና የአሉባልታን ሰንሰለት አጥብቀው የሚያወግዙት የባህል ሀያሲው አቶ ዮሐንስ ወላይሶ ናቸው። ሻምበል ለይኩንም ሆነ ሻምበል ጉተማ የሀገር ባለውለታዎች ናቸው። የሚገባቸውን ክብር ግን አልሰጠናቸውም። የጓዶቹ ሽሙጥ ያስመረረው ለይኩን ከካምፕ ጠፍቶ ወዴት ሄደ? ሕወሃትን ተቀላቀለ። ከዚያስ? ከዚያ ያዋረደውን ሥርዐት ወግቶ ጣለ። ለይኩን እንዲህ ያለውን ውሳኔ እንዲወስን የገፋፋነው እኛው ነን። ለይኩንን በተሳሳተ መንገድ እንዲሄድ የገፋፋነው እኛው ነን። የሻምበል ለይኩን ፍቅረኛ ሳላይሽ ስለ ለይኩን ጠባይና ለምን እንደቀረበችው እንዲህ

ትነግረናለች፡፡ ከሳላይሽ ንግግር ተነስተንም የለይኩን ጥላቻ በሥርዐቱ ላይ ብቻ የተወሰነ አለመሆኑን እንገነዘባለን፡፡ "ሐበሻ የሚባል አይወድም፡፡" ይሄን ዓይነቱን ጥላቻ እንዲያበቅል የገፋፋነው ደግሞ እኛው ነን፡፡ በዳዮቹም እኛው ነን፡፡

ቀደም ሲል በ ያ ትውልድ ስህተቶች ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው ልቦለዱ የባዕዳን ተልዕኮ ባላቸው ገጸባህርያት የበላይነት የተዋቀረ ነው፡፡ ተልዕኳቸውም እንደ ህዝብ ያለንን የአንድነት ታሪክ መናድና አዲስ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም ባህላዊ ትርክት መፍጠር ነው፡፡ አዲስ ትርክት ለመፍጠር ደግሞ የግድ ነባሩን ትርክት ማጥፋት ያስፈልጋል፡፡ የባዕዳንን ተልዕኮ ከሚያስፈጽሙ ገፀባህርያት መካከል ፊያሜታን ጨምሮ ፀሐይ፣ አሸናፊ፣ በላይ፣ ሙሴ፣ ቤላ... ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ገፀባህርያት የሕወሃት ካድሬዎች በመሆናቸው ደርግን ማጥላላት የመጀመሪያው ስራቸው ነው፡፡ ስለ ሳተርን ሆቴል ዋና ተጠሪ ሙሴ ከተጻፈው፦"ከጎንደር በድብቅ በኦፐሬሽን በጣም ልጅ እያለ የተሰደደ ሞሳ ነበር፡፡ዛሬ ዛሬ ክርስቲያኖችም ደርግም ይጨቁኑት እንደነበር ሳያፍር ይናገራል፡፡እንዴት እንደጨቆኑት ያብራራበት ጊዜ የለም፡፡ከጠየቁት 'ምን ይወራል?ምን ይወራል?'ይላል በቀዘዘ ፊት፡፡አዎ የሚወራ የለውም፡፡"(አዳም ፣2008፣ 875)የሀገራችንን ታሪክ ለማጣጣል ሲፈልጉ ደብተራ የፃፈው ማለት ልማዳቸው ነው፡፡ ይህን የእነ ፊያሜታን ሀሳብ ደጋግመው የሚተቹት ደግሞ የባህል ሀያሲው አቶ ዮሐንስ ወላይሶ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጥላቻቸው ሌላ አጀንዳ እንዳለው ያውቃሉ፡፡ ጣታቸውን ደርግ ላይ እና ክርስቲያኖች ላይ መቀሰራቸውም የሀገሪቱን ገጽታ ለማበላሸት ስለሚያግዛቸው ነው፡፡ ደርግና ክርስቲያኖች ለንጽጽር የሚቀርቡ ነገሮች አለመሆናቸው ቢታወቅም፣ ሁለቱን በአንድ ላይ ማያያዛቸው፣ ትንሽ እውነታ ላይ በመመስረት የክርስቲያኖችን ገጽታ ለማጠልሸት ስለሚያግዛቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያኖች ነባሩ ባህል፣ ወግና ልማድ ተጠብቆ እንዲዘልቅ ይፈልጋሉ፡፡ ይሄ ደግሞ እነ ፊያሜታ ላቀዱት የባህል አብዮት ትልቅ እንቅፋት ነው፡፡ የባህል አብዮት ስንል የማህበረሰቡ ወግ፣ እምነት፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ቋንቋ፣... በአጠቃላይ ማህበረሰቡ የኔ ብሎ የሚመካባቸው ሀብቶቹ ላይ የሚደረጉ የማሻሻያ ወይም የለውጥ ሙከራዎች ናቸው፡፡ አንዳንድ የለውጥ ሙከራዎች ታድያ ከማህበረሰቡ ወግና ልማድ ጋር የሚጣረሱ ሆነው ይገኛሉ፡፡

"ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ የእኛ ብቻ ሳይሆን የምዕራብ አውሮፓም ታሪክ የተፃፈው በደብተራዎች ነው፡፡ቄስ ወይም ደብተራ ያልነካው የታሪክ መፅሐፍ የለም፡፡ታሪካችንን ማጣጣል የፈለጉ ማርከሻ መረጃ ሲያጡ ይሄ የደብተራ ታሪክ ነው ብለው ያሽሟጥጣሉ(ከቴም

ተሽሚጠጠ)።"(አዳም፣2008፣23)የእነዚህ ገፀባህሪያት ዓላማ ታሪካችንን ማጠልሸት ብቻ አይደለም። ህዝቡ ከየት እንደመጣ እስኪጠፋው ማወዛገብና ለዓመታት ጠብቆ ያቆየውን ስነምግባራዊ መርህ እንዲጥስ መገፋፋት ነው። አቶ አሸናፊ (የ ዘ ድሬክ ካፌ እና ሬስቶራንት ባለቤት) በዚህ ተግባር ከተሰማሩ ሰዎች መካከል አንዱ ነው። የትዕግስት ሻገር ሬስቶራንት እንዲፈርስ ያላደረገው ጥረት የለም። የትዕግስት ሻገር፣ ዕንቁጣጣሽና የመሳሰሉት ሬስቶራንቶች ደግሞ ሀገርኛውን ምግብና የምግብ አዘገጃጀት ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሳደግ የሚደክሙ ናቸው። እኒህ ሆቴሎች የመንገድ ማስፋቱ እቅድ አካል ሆነዋል። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ፈራሽ ናቸው። "When a nation goes down or a society perishes, one condition may always be found-they forgot where they come from." (አዳም ፣2008፣ 786) ከላይ የቀረበው ጥቅስ ውስጥ ያለው "ታሪኩን የማያውቅ ማህበረሰብ" እነ አሸናፊ ሊሰሩት የሚፈልጉት የማህበረሰብ ዓይነት ነው። እዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ደግሞ ማህበረሰቡን እንደ ማህበረሰብ፣ ሀገሪቱን እንደ ሀገር ደግፈው ያቆሚትን ምሶሶዎች ማፍረስ ያስፈልጋል። የነአቶ አሸናፊና መሰሎቻቸው አጀንዳ ይሄ ነው። ታሪኩን የማያውቅ ተቅበዝባዥ ትውልድ መፍጠር።

ቀደም ሲል፣ ፊያሜታ ሚኒሊክን፣ ቤላ ደግሞ ጅግሳን እንደበደሉ ገልጬ ነበር። ይሁን እንጂ የመጀመሪያ ተበዳዮቹ ፊያሜታ እና ቤላ ናቸው። የፊያሜታ የነጻነት ትግል ከሷ አእምሮ የፈለቀ አልነበረም። የምታደርጋቸው እያንዳንዱ ድርጊቶቿ በአገሯ ልጆች አዛዥነት የሚካሄዱ ነበሩ። ሚኒሊክን ብትወደውም እንኳ እነሱ ስላልወደዱት ብቻ ትታዋለች። የተመረዘችው መጠየቅና ማመዛዘን በማትችልበት ለጋ እድሜዋ ነው። ጮክ ብለው ባይናገሩትም ቤላም ፊያሜታም ተበድለዋል። ልጅነታቸው ተበርዟል። የወጣትነትን በረከት አልተቋደሱም። እድሜያቸውን የጨረሱት ከደርግ ጋር ሲሯሯጡ ነው። ይህንን ቤላም ፊያሜታም በደንብ ያውቃሉ። "ተመልሰን ተፈጥረን እነዛን ሰዎች ማረድ።" (አዳም ፣ 484) የሚለው የቤላ ቁጭት የተቀላቀለበት ዓረፍተነገር ሁሉንም ነገር ግልጥልጥ አድርጎ የሚያስረዳን ይመስለኛል። ፊያሜታ ሚኒሊክን ትወደው ነበር። ራሷንም እሱንም ዋሽታለች። ቤላ እንዲህ ትላለች "ሚኒን በልቧ ልትወደው ትችላለች። ልክ ጅግሳን እንደምወደውና መውደዴን ከሌላ እንደምደብቀው።"(አዳም፣2008፣ 666) ምክንያቱም አእምሮዋ ተመርዟል። ከሚኒሊክ ፍቅር ይልቅ ለአገር ልጆቿ አዳልታለች። ፊያሜታ ክፉ ነበረች፤ ምንም ጥያቄ የለውም። ቤላ ክፉ ነበረች ምንም ጥያቄ የለውም ይሁን እንጂ ክፉ ያደረጋቸው ሌላ ክፉ ሰው ነው።ፊያሜታ ሚኒሊክን፣ቤላ ደግሞ ጅግሳን እንዲበድሉ ያሰለጠናቸው ሌላ ሰው ነው። ያን ሰው ደግሞ

ያሰለጠነው ሌላ ሰው ነው:: ያኛውን ሰው ደግሞ ሌላ ሰው ነው፡፡ ያኛውን ክፉ ሰው ደግሞ...ባዕድ...:: ሰንሰለቱ ቢረዝምም በዳዩን እንዲበድል ያሰለጠነው ሌላ ተበዳይ ነው::

በዚህ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና ካላቸው ገፀባህርያት መካከል አንዱ የሆነው ምኒሊክ በፊያሜታ ቢበደልም እሱ ደግሞ ባለቤቱን ወይዘሮ ሳፍሮን ወይም በሌላ ስሟ ዙፋንን በድሏል:: የመበዳደል አዙሪቱ ማብቂያ የለውም:: ሚኒሊክ እንዴት እንደበደላት ሳፍሮን ራሷ እንዲህ ታጫውተናለች:: "እየቆየ መስከሩና ማጤሱ ሲገርመኝ በላዬ ላይ እንደሚወሰልት በሹሙጥና በአሉባልታ ሰማሁ::" (አዳም፣2008፣348 ) ምኒሊክ የበደለው ሳፍሮንን ብቻ አይደለም:: ንጋትንም በድሏል:: ምኒሊክ ምንም ያህል የሚያሳዝን ሰው ቢሆንም እንኳ ሳፍሮን/ዙፋን ላይ እና ንጋት ላይ የፈጸመውን ስናስብ የምንመልሰው ይቸግረናል:: ለሚኒሊክ እንዘን ለንጋት? ማነው የተጎዳው ይበልጡን? ሚኒሊክ ወይስ ንጋት? ወይስ ሳፍሮን?... ይሁንና ሚኒሊክ ጥፋቱን አልሸሸገም:: ሳፍሮን ላይ የፈጸመውን በደል በአፉ ባይናገረውም አምኗል:: የስንብት ቀለማት ዓለም ከስሩ የተናጋ ነው:: ሁሉም ያለ ርህራሄ ይበዳደላል:: ባልንጀራ በባልንጀራው ላይ ይነሳል:: ፀጋ የሚኒሊክን ፊያሜታ በሚስጥር ነጥቆታል (እህቱን ኮኪትን/እታገኘሁንም አግብቷል):: ሚኒሊክን የከዳችው ፊያሜታ ብቻ አልነበረችም:: ጓደኛው ጭምር ከድቶታል:: ሚኒሊክ እውነተኛ ጓደኛ አልነበረውም:: ችግሩን የሚያዋየው አብሮ አደጉ ሳይቀር ከድቶታል:: ባይተዋርነት (alination) ተሰምቶታል::

ቤላም ተበዳይ (victim) ናት:: በዳዩዋ ደግሞ ሞግዚቷ ተስፋዬ ነው:: የተደፈረችው በአስራ አራት ዓመቷ ነው:: ዓይነቱና መጠኑ ይለያያል እንጂ ሁሉም ገፀባህርያት ተበድለዋል:: ቤላ የፖለቲካውን ዓለም የተቃለቀለችው ከአሳዳጊዎቿና ከማህበረሰቡ ያጣችውን ክብርና ፍቅር ለማግኘት ነው (ልክ አቶ ጉተማ ከማህበረሰቡ ያጣውን ክብር ለማግኘት ጦር ሜዳ እንደዘመተው):: በአስራ አራት ዓመቷ ተደፍራ ለጸነሰች ታዳጊ፣ ፖለቲካ ትልቅ መሸሸጊያዋ ነበር:: የባህል ሀያሲው አቶ ዮሐንስ ወላይሶ ያ ትውልድ ነበረበት ከሚሏቸው ህመሞች ውስጥ "ሰባተኛው ህመማቸው በጣም የግል ጉዳያቸውና ለማንም የማይነግሩት ነው:: በተፈለገ ጊዜ ግን አገራዊ አጀንዳን መሻሪያ ወይም መከለሺያ ሆኖ ይቀርባል:: ግራ ይገባናል::" (አዳም፣2008፣ 429) ቤላ ያደረገችው ተመሳሳይ ነው:: ተስፋዬ ኤርትራ በኢትዮጵያ ተበድላለች ሲሉ ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዱ ነው:: ግን እሱም የአደራ ልጁን በድሏል:: ቤላን ደፍሯል:: ይህም የሚያሳየው መበዳደል የማህበረሰባችን አንዱ ገጽታ መሆኑን ነው:: ተስፋዬ ከሚኖርበት ማህበረሰብ የተለየ ስነልቦና ሊኖረው አይችልም:: ይህ ዓይነቱ የተስፋዬ የሞራል ዝቅጠት

የሀገራችን መልክ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ኤርትራን በድላለች ይላል ተስፋዬ፡፡ በዚህ ሎጂክ ተስፋዬ ጭቁን ነው፡፡ ግን ለተስፋዬ ከንፈር እንመጣለን? ተስፋዬ እኮ ቤላን በድሏል፡፡ ቤላን ደፍሯል፡፡ ለቤላ ከንፈር እንመጣለን? ግን ቤላ እኮ ጅግሳን በድላለች? ግን ለጅግሳ ከንፈር እንመጣለን? ጅግሳም እኮ ሀገሩን በድሏል፡፡ ለቤላ ብሎ ሀገሩን ሰልሏል፡፡ በአጠቃላይ የመበዳደል አዙሪቱ ማለቂያ የለውም፡፡ ምክንያቱም መበዳደል አንዱ ጠባያችን ነው፡፡ ይህ መሰሉ የመበዳደል ሰንሰለት የቤላ እና የሞግዚቷ ተስፋዬ ወይም የሚኒሊክ እና የፊያሜታ ታሪክ ብቻ አይደለም፡፡ በሁሉም ገፀባህርያት ሕይወት ውስጥ ያለ ነው፡፡

ከሁሉም ገጸባህርያት (ከሚኒሊክ ቀጥሎ) እጅግ የምታሳዝነው የምትክ እናት ወይዘሮ ላስታ ናት፡፡ ወይዘሮ ላስታ በደርግ ዘመነ መንግስት የአስራ አራት ዓመት ልጇን በቀይ ሽብር አጥታለች፡፡ ለልጇ ሞት ደግሞ የ ዘ ድሬክ ካፌና ሬስቶራንት ባለቤት አሸናፊ ዋነኛው ተጠያቂ ነው፡፡ አቶ አሸናፊ አሁን የሚጠራበትን ስም ያገኘው አሜሪካን ሀገር ቺካጎ ስቴት ከሄደ በኋላ ነው፡፡ ከሀያ አመታት በኋላ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ንፋስስልክ ውስጥ ዘ ድሬክ የተባለ ካፌ እና ሬስቶራንት ከፍቷል (ልክ የአሜሪካ ቺካጎውን ዘ ድሬክ የመሰለ)፡፡

አሸናፊና ላስታ በዳይና ተበዳይ ናቸው፡፡ በስም ስህተት የተነሳ ምስኪን እናት ልጇን አጥታለች፡፡ መበዳደሉ በደርግ፣ በአሸናፊና በላስታ መካከልም ሊሆን ይችላል፡፡ በተወሰነ ደረጃ የደርግ ታጣቂዎች ስህተትም ነበረበት፡፡ ወንጀለኛው ሳይጣራ "ነጻ እርምጃ" መውሰድ ምንም አይነት ተቀባይነት የለውም፡፡ እዚህ ላይ ጥያቄው አሸናፊ እውነተኛ ታጋይ ነበር ወይ? ነው፡፡ አሸናፊም ልክ እንደ እነ ፊያሜታ ነው፡፡ ሲሮጥ የነበረው የተነገረውን ይዞ ነው፡፡ ፖለቲካዊ ዝንባሌው ከራሱ አእምሮ የፈለቀ አልነበረም፡፡ የጠለቀ እውቀት አልነበረውም፡፡ "ከትምህርቱና ከፖለቲካው ፓምፍሌት ሌላ ያነበበው የለም፡፡ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡" ( አዳም፣2008፣ 425)ፊያሜታ፣ ቤላ፣ አሸናፊ...እና መሰል ፖለቲከኞችም ወደ ትግሉ የገቡት የትግሉ ዓላማ ገብቷቸውና ልባቸውን ፈንቅሎት አይደለም፡፡ የተነገሩትን ይዘው ነው፡፡ የሚሉትን ሰምተው ነው፡፡ ልክ ሳምራዊው "ጥሩ ከሆንክ ቂል ያደርጉሃል፡፡ ብልጥ ከሆንክ ክፉ ያደርጉሃል፡፡"(አዳም፣2008፣404) እንዳለው ነው፡፡ መስፈርቱ ፖለቲካዊ እውቀት አልነበረም፡፡ ክፉ ለመስራት መስፈርቱ ብልጠት ነው፡፡

በተስፋዬ ሞት የተጎዳቸው ላስታ ብቻ አልነበረችም፡፡ ከወይዘሮ ላስታ በላይ የተጎዳው በልጁ ሀዘን ሕይወቱ ያለፈው ባለቤቷ ደረሰ ዋቄ ነው፡፡ ደረሰ ዋቄ ብቻም አይደለም ምትክም ተጎድታለች፡፡ ምትክ የሚለውን መጠሪያዋንም ያገኘችው "ለተስፋዬ ምትክ ሆናልናለችና"

ብለው ነው፡፡ ይሁንና ምትክ እንደ ተስፋዬ ብሩህና መልከ መልካም አልነበረችም፡፡ለዚህ ሁሉ ችግር መፈጠር ዋነኛው ምክንያት አሸናፊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተስፋዬ እንዲገደል ሴራውን ያቀነባበረው እሱ ነው፡፡ ራሱን ለማዳን ሲል ለንጹሕ ታዳጊ ሞት ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ጥፋቱ በጉልምስና እድሜው ጸጸት ውስጥ ቢከተውም በምትክና በቤተሰቦቿ ሕይወት ላይ ያሳደረውን መከራ አይቀንሰውም፡፡ የላስታ ልጅ ተስፋዬ በተገደለበት እለት ሌሎች ስድስት ሰዎች ተገድለዋል፡፡ ለታዳጊው ተስፋዬ ሞት ምክንያት የሆነው አሸናፊ ዛሬም ድረስ ጀግና ተብሎ መጠራት ይፈልጋል፡፡ ዛሬም ድረስ የታጋይ ወግ እንዲደርሰው ይፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ የሰራው ሀጥያት ወንድሙን ገድሎ ዙፋን ላይ እንደወጣው የሐምሌት አጎት ጣዕረሞት እየጎተተ እንቅልፍ ነስቶታል፡፡ "መቼም ይዘገያል እንጂ ከምድር ብናመልጥ ከህሊና፣ ከህሊና ብናመልጥ በሰማይ መጋለጣችን አይቀርም፡፡" (አዳም ፣2008፣ 639) እንዲል ሻምበል ጉተማ፡፡

ወደ ርዕሰ ጉዳዩ ዋነኛ ትኩረት የመበዳደል አዙሪት ስንመለስ አሸናፊ ላስታን በድሏል፡፡ ልጇን ብቻ አይደለም ባለቤቷንም ጭምር አጥታለች፡፡ ይሁን እንጂ ላስታም ሌላ የበደለችው ሰው አለ፡፡ እሱም ባለቤቷ ደረሰ ዋቄ ነው፡፡ ላስታ በደረሰባት ሀዘን ምክንያት ለሁለት አስርት አመታት በብቸኝነት ኖራለች፡፡ ሀዘኗም ብርቱ ነበር፡፡ ለዚህም ሀዘን የዳረጋት የልጇ መገደል ብቻ አልነበረም፡፡ በልጇ ሞት አዝናለች፡፡ ሀዘኗን ብርቱ ያደረገው ግን ተስፋዬ ከተኮላ የጸነሰችው ልጇ ስለነበረ ነው፡፡ የተኮላና የላስታ ግንኙነት የተጀመረው ደረሰ ዋቄን ከማግባቷ በፊት ቢሆንም ከተኮላ መጸነሷን ያወቀችው ከተወለደ በኋላ ነው፡፡ ለባለቤቷ ለመናገር ግን ድፍረቱ አልነበራትም፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ደረሰ ዋቄ የሞተው በልጁ ሞት የተነሳ ሀዘኑን መቋቋም ባለመቻሉ ነው፡፡ በታሪኩ መጨረሻ ላስታ ሲኖዳን ልታገባ በምትሰናዳበት ወቅት ይህንን ክስተት ለልጇ ምትክ መናዘዝ ስለነበረባት አስረድታታለች፡፡ተስፋዬ የተኮላ እንጂየደረሰ ዋቄ ልጅ አልነበረም፡፡ የታመመውም የሞተውም ላልወለደው ልጅ ነበር፡፡ አሸናፊ ላስታን በድሏል፡፡ ልጇን አስገድሎባታል፡፡ ላስታ ደግሞ ደረሰ ዋቄን በድላለች፡፡ ላልወለደው ልጅ ታምሞ ሲሞት ዝም ብላዋለች፡፡ ላስታንም ተኮላ በድሏታል፡፡ ደሃ፣ ባላገር፣ ያልሰለጠነች ናት ብሎ ንቋታል፡፡... ከእነዚህ ትንንሽና ተራ ታሪኮች የምንረዳው የመበዳደል አዙሪቱ ማለቂያ የሌለው መሆኑን ነው፡፡ አንዱ ገጸባህሪ አንዱን ይበድላል፡፡ አንዱ ደግሞ ሌላኛውን ይበድላል፡፡ ለተበዳዩ አዝነን ሳንጨርስ ያኛውም ገጸባህሪ ሌላ ሰው ይበድላል፡፡... አዙሪት መባሉም በዚህ የተነሳ ነው፡፡

ጠቅለል ሲል ከዚህ ታሪክ ውስጥ ልባችን የሚቀረው የልጅ ተስፋዬና የሌሎቹ ስድስቱ ሰዎች ሞት ነው። ይህም ታሪክ እንዲሁ የቀረበ ሳይሆን ሀገራችን በአብዮት ስም የነገ ተስፋዎቿን ለመግደሏ ማሳያ ነው። የእናት የላስታ ለሁለት አስርት ዓመታት በጉስቁልና ማሳለፍ ደግሞ ሀገራችን በድኅረ አብዮት ላስተናገደችው ሀዘን ተምሳሌት ሆኖ የቀረበ ነው።

ለዚህ ርዕስ ሁነኛ ማሳያ ሊሆኑን የሚችሉት ሌሎች ገጸባህርያት ፀሐይ፣ ወርቁ፣ ሮማንና ፍኖት ናቸው። ወርቁ ገጣሚና ሰዓሊ ሲሆን ሮማን ደግሞ ፍቅረኛው ናት። በዚህ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው በዳይ ፀሐይ ሲሆን ከወርቁ ሮማንን ወስዷል። ለዚህም ያነሳሳው በወርቁ ስለሚቀናበት ነው። ለምን እንደሚቀናበት ከጓደኛው በላይ ጋር ባደረገው ምልልስ እንረዳለን።"ትቀናበታለህ እንዴ?

ዝም ብለህአታውራ አቦ።ምኑ ነው የሚያስቀናው?"

"የማትቀና አትመስልም?"(አዳም፣2008፣ 439)

ፀሐይ በወርቁ ላይ የሚቀናበት ልክ እንደ ወርቁ መግጠምና መሳል እየፈለገ፣ መግጠምና መሳል ባለመቻሉ ነው። ፍቅረኛውን ሮማንን የነጠቀውም ለዚህ ነው። በዚህም ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ተበዳይ ወርቁ ነው። ሁለተኛዋ ተበዳይ ደግሞ ሮማን ናት። ምክንያቱም ፀሐይ ሮማንን ያቀረባት ወርቁን ሊጎዳው እንጂ ሮማንን ወድዷት አልነበረም። የፀሐይ ዓላማ የወርቁን ልብ መስበር ነበር። "ሮማን ውስጥ ምንም የለም። የማህፀን ወዟን በየአደባባዩ አርከፍክፋ ጨርሳለች። ይህቺ እንከን የለሽ ውብ ውስጧ እንዴት እንዲህ ባዶ እንደሆነ በሰቀቀን ያስባል።" (አዳም፣2008፣ 454) ይህቺኛይቱ ሮማን የሀገራችን ሌላኛዋ ምሳሌ ናት። ሀገራችን ጥሩ ገጽታ እንዳላት ሁሉ መጥፎ ገጽታ ጭምር አላት። ሀገራችንም በሆነ መልኩ የማህጸኗን ወዝ በየአደባባዩ አርከፍክፋለች። የላስታ ልጅ "ተስፋዬን" ገድላለች። ተስፋዬ መባሉ በራሱ ሌላ አንድምታ ያለው ይመስላል።

የወርቁንና የሮማንን ታሪክ ሳስብ የፊያሜታና የሚኒሊክ ታሪክ ትዝ ይለኛል። ፊያሜታ ሚኒሊክን የምትወድ እየመሰለች ከጓደኛው ፀጋ ጋር ትወጣ እንደነበረው ሁሉ ሮማንም ወርቁን የምትወድ እየመሰለች ከፀሐይ ጋር ትወጣለች። በዚህም ታሪክ ውስጥ ፀሐይ ወርቁን ሲበድል፣ ሮማን ደግሞ እምነት በማጓደል ወርቁን በድላለች። በጣም የሚያሳዝነው ግን ወርቁም ሌላ ሰው በድሏል። ወርቁም የትምህርት ቤት ጓደኛውን ፍኖትን በድሏል። ፍኖትን የተዋት ለሮማን ብሎ ነበር። ምክንያቱም ሮማን ከፍኖት በላይ መልከመልካም ናት። የሚያሳዝነው ግን ፍኖትም ስፓኒሹን ባለቤቷን ዶን ሪካርዶን በድላለች።... በዚህ ታሪክ ውስጥ ከፀሐይ ተነስቶ ወደ ሮማን–

ከሮማን ወደ ወርቁ– ከወርቁ ወደ ፍኖት– ከፍኖት ወደ ዶን ሪካርዶ– የሚወርደው የመበዳደል ታሪክ ለዚህ ርዕስ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። ወርቁን ቀድማ የከዳችው ሮማን ናት።"እንለያይ" ብላ ለመናገር ግን ድፍረቱ አልነበራትም። ለዚያም ይመስላል የእንለያይ ጥያቄው ከእርሱ እስኪመጣ ስትበድለው የነበረው። በመጨረሻ ግን ለፀሐይ የነበራት ፍቅር እየበረታ ስለመጣ “ደህና ሁን” ብላ ልትሰናበተው ትወስናለች። ይህም ከምንም በላይ የወርቁን ስሜት የጎዳ ክስተት ነበር።"ከሮማን ጋር መለያየታችን ብዙ ጊዜ ቢያልፈውም ስለ ሰበቡ የበለጠ ለማወቅ ማሰቤን እንደስራም እቆጥረዋለሁ። ቀድማ እሷእንደ ከዳችኝ፣በመንፈስ ከእኔ እሷ ቀድማ ውሳኔ ሰጥታ እንደተሰናበተችኝ መገንዘቤ ውስጤን እንደ ብል ይበላዋል።"(አዳም፣2008፣675)ሮማን ፣ከቤላና ከፊያሜታ የተለየች አይደለችም።ወርቁን የበደለችው ልክ ፊያሜታሚኒሊክን እንደበደለችው ነው።ቅናት ፣ምቀኝነት፣አጉል ዘመናይነት የፊያሜታ፣የቤላ ፣የሮማንና የሳላይሽ ጠባይ ነው።

ታሪኩ በሕወሃት ካድሬዎች የበላይነት የተዋቀረ ነው። ፀሐይና በላይ የግል ጋዜጣ አዘጋጆች ናቸው። "ፀሐይና በላይ የጠሉትን በእነሱ ዐይን ሞገስ ያላገኘውን ጥርሳቸው ካስገቡት የአዲስ አበባ ሕዝብ ሁሉ እንዲነክሰውና እንዲሸሸው ማድረግ ይችላሉ።እነሱ ያገለሉትን የአዲስአበባ ሕዝብ እንዲያገለው የማድረግ ተሰጥኦና ሥልጣን አላቸው።"(አዳም 440) ፀሐይና በላይ የዘመኑ የመገናኛ ብዙሃን ሰዎች ወኪሎች ናቸው ።ጭራ ይዘው ሕዝብ የማሳት ተሰጥዖ አላቸው በሬ ወለደ ቢሉ ይታመናሉ።ይሄ አንድም የእኛን በመረጃ አቀባበል ረገድ የሚስተዋል

ቀርነት ሲያመለክት በሌላ በኩል ደግሞ ከራሱ ከመገናኛ ብዙኃን አንዳንድ ባለሞያዎች በኩል የሚስተዋለውን ስርዓት አልበኝነት ያሳያል። መረጃን ጠይቆና መርምሮ መቀበል ራሱን የቻለ የንቃተ ሕሊና መመዘኛ ነው። መረጃ ስለተነገረ ብቻ ሙሉ በሙሉ እውነትነት አለው ማለት አይደለም። እኒህ ሁለት የመገናኛ ብዙኃን ሰዎች አንድ በስዕል ሥራ የሚተዳደርን ወጣት ስም ሊያጎድፉ ሌት ተቀን ሲሰሩ እንመለከታለን። አላማቸውም ወጣቱን በአንባቢያንና በኪነት አፍቃሪያን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጣ ማድረግ ነው። ግጥም ሲጽፍ “ትርጉም ነው” ይላሉ። ሲስል “ገብረ ክርስቶስን ለመምስል ይሞክራል” ይላሉ። ሙሉ በሙሉ ባይሳካለቸውም እንኳ ካስጠረጠሩት በቂ ነው። ፀሐይ ራሱ “ጥርጣሬ ሕግ የሚሆንበት አገር ነው ያለነው።”(አዳም፣2008፣443) ይላል። በሮማንና ወርቁ ታሪክ ውስጥ ብቅ የምትለው ሌላኛዋ ገፀባህሪ ዘውዲት ናት።ዘውዲት የሮማን ዘመድ ናት።ስዕልአስተምራት ብላ ወደ ወርቁ ያመጣቻት ሮማን ናት። ዘውዲት ቀስ በቀስ ከሰዓሊው ወርቁ ጋር ጓደኛሞች ከሆኑ በኋላ ሚስጥሯን ትነግረዋለች። ዘውዲት የወላጆቿን ጓደኛ ናሆምን እንደወደደችውና እንደጸነሰች ትነግረዋለች።

(ዘውዲት) “አንድ ነገር ልጠይቅህ?”

“እሺ” (ወርቁ)

“ሮማን ብታረግዝ ዞር በይ ትላታለህ?”

“እንጃ ለመውለድ አላሰብንም....ምነው አርግዘሻል?”

በቃል ሳትመልስልኝ በአወንታ ዐይነት አየችኝ:: ደነገጥኩ::

ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና ወዲያ ወዲህ አልኩ::

“አሁን ቅድም የዘገየሁት ማርገዜን ልነግረው ነበር:: ታድያ ስነግረው ሁለተኛ እንዳላይሽ አለኝ:: (አዳም፣2008፣ 224)

ዘውዲት ጸንሳ ፍቅረኛዋ ስለካዳት ራሷን ያጠፋች የአስራ ስምንት አመት ወጣት ናት:: በዚህም ታሪክ ውስጥ ናሆም በዳይ ሆኖ ተገኝቷል:: በደሉም ሁለት ዓይነት ነው:: የመጀመሪያው ባለትዳር ሆኖ ሳለ በእድሜ ከማትመጥነው ታዳጊ ጋር ፍቅር መጀመሩ ነው (ከዘውዲት ጋር ፍቅር የጀመረው የአስራ አራት ዓመት ታዳጊ በነበረችበት ወቅት ነው::ሁለተኛው ደግሞ ስትጸንስ እንዳላይሽ ብሎ ማባረሩ ነው:: ይህም በተዘዋዋሪ ራሷን ለማጥፋቷ ተጠያቂ ያደርገዋል:: ይህቺ ዘውዲት በሀገራችን ትመሰላለች:: እነ ናሆም “ሀገራችን በቂ ነገር አልሰጠችንም” ብለው በገዛ ሀገራቸው ላይ ያሴሩ ባንዳዎች ናቸው:: የዘውዲት ጸንሻለሁ ስትል “ደግሜ እንዳላይሽ” መባሏም ሀገራችን ያመጹባት ልጇን “ያለኝ ልስጣችሁ” ስትል “አንፈልግሽም የራሳችንን ሀገር እንፈጥራለን” ብለው ከገፏት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ይመስላል::

የስንብት ቀለማት የመበዳደል ታሪኮችን መለስ ብለን ስንቃኝ አንዳች ሰንሰለታዊ ቅርጽ እንዳላቸው እንገነዘባለን:: ፊያሜታ ሚኒሊክን፣ ሚኒሊክ ንጋትና ሳፍሮንን፣ ቤላ ጅግሳን፣ ቤላን አሳዳጊዋ፣ ሮማን ወርቁን፣ ሮማንን ፀሐይ፣ ወርቁ ፍኖትን፣ ፍኖት ደግሞ ባለቤቷን፣ ናሆም ዘውዲን፣ ጅግሳ ሀገሩን፣ አሸናፊ ላስታን፣ ላስታ ደረሰ ዋቄን ...አንዱ ተበዳይ ሌላ ተበዳይ አለው:: ከምንም በላይ የሚያሳዝነው ደግሞ የተበዳደልነው እርስበርሳችን መሆኑ ነው:: ፊያሜታ ሆነች ቤላ፣ ወርቁም ሆነ ፀሐይ...ኢትዮጵያዊያን ናቸው::

ይሄ ስዕል ደሞ... 1700 ዓ.ም አካበቢ የተሳለ ነው:: ስለ አንድ በቀስት ስለተወጋ ጭልፊት ነው:: ... እና አንድ ጭልፊት ጎኑን በቀስት ተመቶ ከሰማይ ላይ እየወደቀ እያለ ዞር ብሎ የተወጋበትን ቀስት ሲያይ፣ የራሱ ዐይነት ላባ ተሰክቶበት አየ:: ገባህ? ‘በወገንህ እጅ እንደ መጥፋት ቀላልና ከባድ ነገር የለም ማለት ነው::

በልምዱ አገሬ እያለሁ አይቼዋለሁ። ቤት አዋቂዎች ስለሆኑ ከጠላት ጋር ካበሩ በቀላሉ ድራሽህን ያጠፉታል። አንጀት የሚበላ አጠፋፍ ነው። (አዳም፣2008፣ 243- 244) (ሰረዙ የእኔ ጭማሪ ነው)

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደተሞከረው የስንብት ቀለማት የባዕዳን ተልዕኮ ባላቸው ገፀባሕርያት የበላይነት የተዋቀረ ነው። ከሰረዙ ላይ ለመረዳት እንደምንችለው ከጠላት ጋር ካበሩ ድራሽህን ያጠፉታል የሚለው ለእነ ፊያሜታ፣ ቤላ፤ አሸናፊ፣ ሙሴና ለመሳሰሉት የተነገረ ነው። እኒህ ገፀባህርያት የባዕዳንን አጀንዳ ይዘው የገዛ ሀገራቸውን እንዲሁም የበቀሉበትን ማህበረሰብ በድለዋል። ሰው ነንና ተመሳሳይ አመለካከት፣ የፓለቲካ ዝንባሌና የታሪክ አቀባበል ባይኖረንም እንኳ የወንድም እህትማማቾችነታችን እውነተኛነት ግን ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። የእኛ መበዳደልም በንስሩና በቀስቱ ላባ ይመሰላል። የተጠፋፋነው እርስበርስ ነው።

## 3.2.3 የተስፋ ጭላንጭሎች

የስንብት ቀለማት ዓለም በወከባ፣ ግጭት፣ ምቀኝነት፣ ሴራ፣ ...የተሞላ ነው። አንዱ ገጸባህሪ ከሌላኛው ጋር ሲታገል፣ አንዱ በአንዱ ላይ ሴራ ሲተበትብ፣...ይታያል።ታዲያ ይሄ ሁሉ ግጭትና ወከባ ማብቂያ አለውን? ተስፋ በስንብት ቀለማት ውስጥ “እንዲህ ነው ወይም እንዲያ ነው” ብለው የሚደመድሙት ነገር አይደለም። የግጭቶቹ መርገብ የሚያስከትለው አሉታዊም አዎንታዊም ተጽዕኖ አለ። ለጭላንጭል ተስፋዎች መፈንጠቅ በምክንያትነት የሚጠቀሱትም እነዚሁ የግጭቶቹ መርገብ የሚያስከትሏቸው አዎንታዊ ተፅዕኖዎች ናቸው።

ሚኒሊክ የሞተው ቀስ በቀስ ነው። ሲሞት ሰውነቱ ከእግሩ ጀምሮ እስከ ወገቡ ድረስ በድን (ፓራላይዝ) ሆኖ ነው። ይህንን ታሪክ ስናነብ የስንብት ቀለማቱ ምኒልክ አሟሟት ከአጼ ምኒልክ አሟሟት ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው እንታዘባለን። ግጥምጥሞሹ ድንገቴ ነው ወይስ አንዳች ጭብጣዊ ፋይዳ አለው? ብለን እንድንጠይቅም ያስገድደናል። በታሪክ እንደምናውቀው ደግሞ አጼ ምኒልክ በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ግንባታ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ከተወጡ ጥቂት መሪዎች ውስጥ አንዱ ሲሆኑ፣ የጠላትን ወረራ በተሳካ ሁኔታ ከመመከት ጀምሮ አዳዲስ የስልጣኔ ጅማሮዎችን ወደ ሀገር ቤት በማስገባት ይታወቃሉ። ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት በሚተረከው ትርክት ውስጥ ደግሞ ሁለት ዓይነት መልክ አላቸው። አጼ ምኒልክ በአንዱ ወገን በኩል እንደ ጀግና በሌላኛው ወገን በኩል ደግሞ እንደ ጨካኝ መሪ ይታያሉ። በተለይም

በኤርትራውያን ታሪክ ውስጥ መልካም ስም የላቸውም። ለኤርትራ በጣልያን አገዛዝ ስር መቆየት እንደ ዋነኛ ምክንያት ይታያሉ። በመሀል ሀገር የታሪክ ጸሀፍት በኩል ደግሞ "አጼ ምኒልክ አቅም አጥተው ነው እንጂ ኤርትራን አሳልፎ የመስጠት ፍላጎት አልነበራቸውም" የሚል ማስተባበያ ይቀርባል። ከአድዋ ማግስት የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን ክፉኛ እየፈለገ እስከ አምሳዎቹ አጋማሽ በጣልያን አገዛዝ ስር መቆየቷ፣ ምኒልክ ፍያሜታን ክፉኛ እየፈለገ በሌሎች መቀደሙ ጋር አንዳች ትስስር ያለው ይመስላል።

ለአብነት ያህል የምኒልክ መሞት አወንታዊም አሉታዊም ጎኖች አሉት። አሉታዊው የምኒልክን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእነ ፊያሜታ መሸነፉን የሚያረዳ መሆኑ ነው። ምኒልክ እድሜውን በሙሉ የወደዳትን ፊያሜታን አጥቷል። ይህም በእርሱና በልጆቹ እንዲሁም በባለቤቱ ሕይወት ላይ የሚያሳድረው ሀዘን አለ። አሟሟቱ እንግዳ መሆኑም ሀዘኑን ያባብሰዋል።

አዎንታዊው ጎኑ ደግሞ በንጋትና በሳፍሮን መካከል ወዳጅነት እንዲመሰረት እንዲሁም የንጋት ልጅ ደመወዝ ከእህቶቹ ጋር እንዲገናኝ እድል መፍጠሩ ነው። እነ ፊያሜታ ምኒልክ ሞቶም እንኳ እጃቸው አላረፈም። ፊያሜታ ምኒልክ ከሌላ ሴት ልጅ እንዳለው ባለቤቱ ሳፍሮን እንድታውቅ አድርጋለች። ነገሩ ግን ባሰበችው መንገድ አልሄደላትም። የሳፍሮንን ሕይወት ምስቅልቅሉን ልታወጣ ብታቅድም በንጋትና በሳፍሮን ቅንነት ምክንያት ሴራው ከሽፎ ወደ ደስታ ተለውጧል። ይሄ የፊያሜታ የከሸፈ ሴራ ነው።

ቤላም በተመሳሳይ የምኒልክን ልጅ ደመወዝን ለመስበር ያደረገችው ሙከራዋ ሲከሽፍባት እንመለከታለን። ደመወዝ፣ በፊያሜታና በቤላ በሚመራው "ሴቶችና ህጻናት" ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ሲሰራ ከቆየ በኋላ የሰራበትን ገንዘብ ሊቀበል ወደ ቢሯቸው ሲሄድ ከፊያሜታ የወንድም ልጅ ኤደን ጋር ይተዋወቃሉ። ይሁን እንጂ በወቅቱ በቢሮ ውስጥ የነበረችው የማናቀፍ ደዌ የተጠናወታት ቤላ በመሃላቸው ልትገባ ስትሞክር ይታያል። "ስልኩን ዘግቼ ወደ በረንዳ ወጣሁ። ደመወዝ የተባለው ልጅና ኤደን ተጠጋግተው ቆመው ያወራሉ። የመጠባበስ አጠጋግ ይመስላል። ኤደን የፊያሜታ የወንድሟ  ልጅ ናት።" (አዳም፣2008፣ 841) በዚህ ጥቅስ ሁለት ነገሮችን እንረዳለን። የመጀመሪያው የቤላ ወጥመድ መክሸፉን ነው። ይሄኛው ምኒልክ ድንጉጥ አይደለም። እንደ ምኒልክ አይርበተበትም። ሁለተኛ ደግሞ በእነ ፊያሜታ ያልሰመረው ፍቅር በምኒልክ ልጀ ደመወዝና በፊያሜታ ወንድም ልጅ ኤደን መካከል የሰመረ

መስሎ መታየቱ ነው። ፍቅር ብቻ ሳይሆን ጓደኝነቱም ሲሰምር እናያለን። የቤላና የምኒልክ ወዳጅነት እስከዚህም ነበር። ቢቀራረቡም እንኳ የእውነት አልነበረም። አሁን ግን በልጆቻቸው ሰምሯል። የቤላ ልጅ ዘካርያስና የምኒልክ ልጅ ደመወዝ ጥሩ ጓደኛሞች ሆነዋል። ቤላንና ምኒልክን ያቀራረባቸው ፖለቲካዊ ዝንባሌ ነው። ዘካርያስንና ደመወዝን ግን ያቀራረባቸው እግር ኳስ ነው። ስፖርት ደግሞ የሰላም፣ የፍቅርና አንድነት ምሳሌነት አለው። እነዚህም የወዳጅነት ምልክቶች በኤርትራ ተወላጆች እና በኢትዮጵያውያን መካከል አዲስ ምዕራፍ እየተዘረጋ መሆኑን ያሳያሉ። ሌላ ምሳሌ እንጨምር፦ “አይዳ… አስመራ ተወልዳ በአስራ ሁለት አመቷ እዚህ ብትመጣም፣ ‘የምትወጂው ዘፈን የማንን ነው?’ ብትባል የአለማየሁ እሸቴ ‘አዲስአባ ቤቴ’ ነው ትላለች።” (አዳም፣2008፣ 845) አይዳ ተወልዳ ያደገችው አሥመራ ይሁን እንጂ ለመሃል ሀገሩ ኪነጥበብ ቀና አመለካከት አላት። ይህም ከእነ ኢዛና፣ ቹቹ፤ ኤደን… ወገን ያስልፋታል። በሕወሃት ካድሬዎች የበላይነት በተዋቀረ የስንብት ቀለማት ዓለም ውስጥ እንዲህ ዓይነት ገፀባህርያት የብሩህ ነገ ፋናወጊዎች ናቸው። በአይዳ፣ አዴን፣ ዘካርያስ፣ ደመወዝ፣ ሮቤል፣ ኢዛና፣ ቹቹ…ውስጥ ተስፋ አለ። ምክንያቱም የአዲሱ ትውልድ አባላት ናቸው። ከአዲሱ ትውልድ ይህን መሰል ነገር መመልከት ደግሞ ተስፋ ሰጭ ነው። ለምሳሌ ደበሌ የተባለው ወጣት “አሸባሪ” የሚል ታርጋ ተለጥፎለት ታጣቂዎች ሊያስሩት ሲመጡ የኢትዮጵያን አንድነት ሲያበስር እናያለን። “ኢትዮጵያ አንድ ናት! ባንዶች ይወድማሉ! ለከሀዲዎች አንገዛም! ኢትዮጵያ ታሸንፋለች!” (አዳም፣2008፣865 ) ሮቤል ገብረሕይወት ለኤርትራዊያን ጠቅለል ሲልም ለሰሜን ተወላጆች አዲስ ፖለቲካዊ እሳቤ ማሳያነት የቀረበ ገጸባህሪ ነው። ወጣቱ የባዕዳን የከፋፍለህ ግዛ አጀንዳ የገባውና ምድር ላይ የወረደው ሀቅ ኤርትራዊም ሆነ ኢትዮጵያዊ ከአንድ ማህፀን የበቀለ የስጋና የመንፈስ ዝምድና ያለው ሕዝብ መሆኑን ያበስራል። ሮቤል በፖሊስ እጅ ተይዞ ከርቸሌ መውርዱም መሪዎቻችን ይህንን እውነታ ፈጽሞ እንዳልወደዱት ማረጋገጫ ነው።

ሌላው ወገግ ያለው ተስፋችን ላይ ግርዶሽ የሚሆንብን አጉል ዘመናዊነት ነው። አጉል ዘመናዊነት ሌላኛው የስንብት ቀለማት አንዱ ገጽታ ነው። በተለይም አንዳንዶቹ ገፀባህርያት በዚህ ደዌ ተጠቅተዋል። ሮማን የእነዚህ ገፀባሕርያት ተጠሪ ናት ማለት ይቻላል። " ሮማን በአሜሪካ ኤሊኖ ስቴት ቺካጎ ከተማ ከባድ ዝናብ ሲጥልትሰማለች ።የአባቴና የእናቴ ሀገር ሮቤ ወደ ምድር ዕምብርት ብትሰምጥ አትሰማም።ብትሰማም ግድ የላትም።"(አዳም፣2008፣208) ይህን የሚለው ወርቁ ነው። ወርቁ የሮማንን መፍቅሬ አሜሪካ አጥብቆ ይተቻል።የሚያሳዝነው ደግሞ ሮማንን የፈጠርናት እኛው ነን። እንደ ሆሊውድ ተዋንያን መናገር፣ እንደ ሆሊውድ

ተዋንያን መልበስ፣ እንደ ሆሊውድ ተዋንያን መራመድ፣... የሮማን የስልጣኔ መገለጫዎች ናቸው:: በአጭሩ ሮማን ራሷንም ሀገሯንም አትወድም:: ሮማን የእነ ፊያሜታ አዲስ ቅጅ ናት:: የሮማን ስልጣኔ ወደ ውጭ አንጋጦ ማየት ነው:: የባዕዳንን የአኗኗር ዘይቤና ፍልስፍና ሙሉ በሙሉ መገልበጥ:: ወደ ውስጥ መመልከት የወርቄ የኪነት ፍልስፍና ነው:: ወደ ውስጥ ሲባል አንድም ወደ ሀገርኛው ወደ ራሳችን ኪነጥበብ አንድም ወደ ውስጣችን ማለቱ ነው:: አንድ ከያኒ ወይም ግለሰብ የራሱን ኀልዮ (idea) ለመፍጠር ከፈለገ ወደ ውስጥ መመልከት አለበት ብሎ ያምናል:: ይሄን የገብረ ክርስቶስን ግጥም ፍልስፍና ሥራዎቹ ውስጥ ደጋግሞ ማንጸባረቁም በዚህ የተነሳ ነው::

አለ በውስጣችን
እውነት ፍፁም ሆና የምታበራበት
ደግሞም ማወቅ ማለት
ከውጭ ያለውን ሄዶ ከመፈለግ
ከውስጥ ያበራውን እንዲወጣ ማድረግ (አዳም፣ 2008፣ 676)

ወርቄ ሰዓሊ ብቻም ሳይሆን ገጣሚም ነው:: ከስዕሎቹ ግርጌ ግጥሞችን ይጽፋል:: የግል ጋዜጣ አዘጋጁ ፀሐይ ደግሞ በወርቄ የተፈለሰፈውን አዲስ የኪነት ፈለግ ለማጣጣል ከሚረባረቡ ግለሰቦች መካከል አንዱ ነው:: ለፀሐይ፣ ወርቄን መተቸት የዘወትር ሥራው ነው:: የኢዛናንና የወርቄን ገጽታ ማበላሸት የፀሐይና የጓደኞቹ የዘወትር ሥራ ነው:: አፍረው ተሸማቀው እንዲሸሹ በሂስ ስም የስድብ ጋጋታ ያወርዱባቸዋል:: አቶ ዮሐንስ ወላይሶ ወርቄንና ኢዛናን ከሚከላከሉ ምሁራን መካከል አንዱ ናቸው:: ይሁን እንጂ ተስፋችን ላይ ግርዶሽ የሚጥል አሳዛኝ ክስተት ይፈጠራል:: አቶ ዮሐንስ ወላይሶ በድንገተኛ የመኪና አደጋ ያርፋሉ:: ይህም የአቶ ዮሐንስ አሟሟት “ደግ አይበረክትም” እንድንል ያደርገናል::

ሌላኛው በስንብት ቀለማት ውስጥ የታየው ደማቁ የተስፋ ጭላንጭል የምትክ ማኩታን መጸነስ ነው:: ምትክ የስንዝሮን (የመንኮቢያውን) ልጅ ማኩታን ጸንሳ ትወልዳለች:: ማኩታ ማለት ደግሞ አምሐ ማለት ነው::ስጦታ::ልጅ የተስፋ ምሳሌ ነው:: ንጋት ደመወዝን ስትወልድ ደስተኛ አልነበረችም:: አልቅሳለች:: መከዳቷ አንገብግቧታል:: ይሄን የታዘበው ሳምራዊው የተባለው ውሻ “ልጅ ወልዳ ታለቅሳለች:: ተስፋ ወልዳ፣ በተስፋዋ ታለቅሳለች::” (አዳም፣2008፣406) ይላል:: ምትክ የጸነሰችው መለኮታዊ ሀይል ካለውና ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት በላይ ከኖረው ስንዝሮ ነው:: መንኮቢያው ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ኖሯል:: ልጁ ማኩታ ደግሞ ለተጨማሪ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት የመኖር

እድል አለው። ይሄም አንድም ኢትዮጵያ ለተጨማሪ አምስት ሺህአምስት መቶ ዓመታት ወደ ሚያቆያት አዲስ የዘመን ምዕራፍ እየተሸጋገረች ለመሆኑ ሌላ መንገሪያ ነው።

ምትክ የሚቹ ወንድሟ የተስፋዬ እንዲሁም የቅድስት ድንግል ማርያም ተምሳሌት ናት። ቅድስት ድንግል ማርያም የአለም መድኅን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን ጸንሳ ዓለምን ከዘላለማዊ ሀጽያት እንዳዳነችው ሁሉ እሷም ለሦስት ሺህ ዘመን ከሀገር ሀገር ሲንከራተት የኖረውን የስንዝሮን ልጅ ማኩታን ትጸንሳለች። እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና አስተምህሮ ኢትዮጵያ የቅድስት ድንግል ማርያም የአስራት ሀገር ናት። ልጇን ይዛ በተሰደደች ዘመን ለሦስት ዘመን እንዳረፈችባት፣ ወደ ሀገሯ ስትመለስም ማርና ወተት ይፍሰስብሽ ብላ እንደመረቀቻትና መቼም እንደማትረሳት ቃል እንደገባችላት ይታመናል። ይሄን እንድንል የሚያነሳሳን ደግሞ የዶ/ር ዮሴፍ ወደ ምትክ ሕይወት በድንገት መምጣት ነው። ዶ/ር ዮሴፍ ማኩታን ጸንሳ እስክትገላገል በአጃቢነት፣ በተንከባካቢነትና በአዋላጅነት ያደረገላት ትብብር ከመጽሐፍ ቅዱሱ ዮሴፍ ጋር ያመሳስለዋል። ይህም ታሪክ ምትክ የማርያም ተምሳሌት ነች የሚለውን ሀሳባችንን ያጠናክርልናል። በማርያም መወከሏም በመንፈሳዊ ፋይዳነት የገባ ሳይሆን መድኃኒት ወለደችልን ለሚለው ታሪክ ተምሳሌታዊ አገላለጽ ነው።

የስንብት ቀለማት ወደ አዲስ ምዕራፍ እየተሸጋገረች ያለች ኢትዮጵያን ያሳያል። ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሸጋግሯት ደግሞ አዳዲሶቹ ትውልዶች ናቸው። አሮጌው ትውልድ ሲሰናበትና ከዋናው ታሪክ ሲገለል እንዲሁም አዳዲሶቹ ብቅ ብቅ ሲሉና የበላይነቱን ሲረከቡ እንመለከታለን። በፊያሜታ ምትክ የወንድሟ ልጅ ኤደንን እንመለከታለን። በቤላ ምትክ ልጇ ዘካርያስ ይመጣል። ሚኒሊክ ቢሞትም ደመወዝ ይነሳል። ተኮላና ጀማነሽ ሊወልዱ ያቅዳሉ። ንጋትና ሳፍሮን ጓደኛሞች፣ ደመወዝና ኤደን ፍቅረኛሞች...ይሆናሉ። ደበሌ ወይም በሌላ ስሙ ሮቤል ገብረ ሕይወት ይፈታል። ቼቼ ተብታባነቷ ይለቃታል... ሴተኛ አዳሪነቱን ትተወዋለች... ላ ጎፈሬ የሚባል ፀጉር ቤትም ትከፍታለች። ላስታና ሲኖዳ ይጋባሉ። የላስታ የጉልት ሕይወትም ያበቃል። በዚያ ፋንታ ሱቅ ይከፈትላታል።...

የስንብት ቀለማት አጨራረስ ሜሎድራማዊ (melodramatic) ድምጸት አለው። ክፉዎቹ ገፀባህርያት የእጃቸውን ያገኛሉ። ለዘውዲት ሞት ተጠያቂ የሆነው ናሆም ይታሰራል።የኀብስትንና የዮሴፍን ትዳር ያመሳቀለችው ሳላይሽ የእጇን ታገኛለች፣ የእሷም ፍቅር ይበተናል። ለይኩን አገር ጥሎ ይጠፋል። በክፉዎቹ ገፀባህርያት መካከል አለመስማማት ይፈጠራል። በፀሐይና በበላይ መካከል ተቃርኖዎች ይስተዋላሉ። ፊያሜታና ቤላ ይቃቃራሉ።

የአሸናፊ ሬስቶራንት ላይ የቃጠሎ አደጋ ይፈጠራል፡፡ ፀጋ ፊያሜታን ይርቃታል፡፡ የቤላና የፊያሜታ ሴራዎች ደጋግመው ይከሽፋሉ፡፡ ቤላና ፊያሜታ በመንፈስ ይራራቃሉ፡፡

የስንብት ቀለማት በስምንት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ በተለያየ ቀለም ተሰይሟል፡፡ የቀለማቱ ፋይዳ ምንድን ነው? ስለ ልብወለዱ ጭብጥ የሚነግሩን ነገር አለን? ሊኖርም ላይኖርም ይችላል፡፡ ምን ማለቴ እንደሆነ ላብራራ፡፡ የቀለማቱ ውክልና ከጭብጣዊ ፋይዳው ይልቅ ቴክኒካዊ ፋይዳው ይደምቃል፡፡ ለምሳሌ አንዱ ምዕራፍ በጥቁር ቢወከል ከጭብጣዊ ውክልናው ይልቅ ቴክኒካዊ ፋይዳው ይጎላል፡፡ በጥቁር ሥር ጠቆር ያለ የሚጫሙ፣ ጠቆር ያለ የሚለብሱ፣ ጠቆር ያለ ነገር የሚጠጡ፣ ጠቆር ያለ መሃረብ የሚጠቀሙ፣ ጠቆር ያለ መነፀር የሚያደርጉ፣ ጠቆር ያለ መኪና የሚያሽከረክሩ፣ … ገፀባህርያትን መመልከት የተለመደ ይሆናል፡፡ ሌላኛው ምዕራፍ በሰማያዊ ቢወከልም ተመሳሳይ ቴክኒካዊ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ሰማያዊ ህንጻ፣ ሰማያዊ መኪና፣ ሰማያዊ ምንጣፍ፣ ሰማያዊ መጋረጃ፣ ሰማያዊ ሶፋ፣ ሰማያዊ ግድግዳ፣ ሰማያዊ ሰማይ፣… ማየት የተለመደ ይሆናል፡፡ ይሄ ማለት ታድያ ቀለማቱ ሁልጊዜ የተለየ ጭብጣዊ ፋይዳ ይኖራቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ደራሲው ሆን ብሎ ለመቼትና ገፀባህርይ አሳሳል ስምረት የመረጠው ስልት ነው፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ጨርሶ ጭብጣዊ ፋይዳ የላቸውም ማለትም አይደለም፡፡ አንዳንድ ቀለማት ከገፀባህርያቱ ሁኔታና ታሪክ ጋር ስምም የሆነ ተምሳሌታዊ ፋይዳ እናስተውልባቸዋለን፡፡ ተራ በተራ እንመልከታቸው፡፡ የኔ ትኩረት ጭብጥ በመሆኑ ቴክኒካዊ ፋይዳዎችን በዋናነት አይመለከትም፡፡

ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ በነድ ተወክሏል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናት መዝገበ ቃላት ነድ ማለት “የእሳት ነበልባል፣ የእሳት ላንቃ” እንደማለት ነው፡፡ ለምን በነድ ተወከለ? በዚህ ክፍል ውስጥ ሁሉም ገጸባህርያት ማለት ይቻላል ወጣቶች ናቸው፡፡ አቶ ዮሐንስ ወላይሶ፣ ቤላ፣ ተኮላ፣ ፊያሜታ፣ ጀማነሽ፣ ምኒልክ፣ ጅግሳ፣…በዚህ ክፍል ውስጥ ወጣቶች ናቸው፡፡ ወይም ደግሞ የሚተረከው በወጣትነታቸው የፈጸሙት ታሪክ ነው፡፡ ወጣትነት ደግሞ ብዙ ጊዜ ከእሳት ላንቃ ወይም ነበልባል ጋር ተያይዞ ይጠራል፡፡ ወይም በዚሁ ይመሰላል፡፡ ምናልባትም በነድ መወከሉ ይህንን ሀሳብ ለማድመቅ ታስቦ የገባ ይመስላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነድ የተኮላ ባለቤት የጀማነሽ ልብሶችና የአቶ ዮሐንስ ወላይሶ መሃረቦች ቀለም ነው፡፡

ምዕራፍ ሁለት በአረንጓዴ ቀለም ተወክሏል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ አረንጓዴ ቀለም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከአንድም ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ አረንጓዴ የዘውዲት ዐይኖች ቀለም ነው፡፡ ወጣቱ ሰዓሊና ገጣሚ ወርቁ ዕንቁ ባሕርይ አረንጓዴና ውብ ዐይኖች ያላት ኢትዮጵያዊት ሳይ

ለመጀመሪያ ጊዜ ነው እያለ ውስጥ ውስጡን ሲደነቅ እንታዘባለን፡፡ ዐይኖቿ ውስጥ ንጽህና፣ ልጅነት፣ የዋህነት፣ ብሩህነት፣ ...እንደሚነበብ ይነግረናል፡፡ የቀለሙም ጭብጣዊ ፋይዳ ይህንኑ የዘውዲት ንጹህ ተፈጥሮ መንገር ይመስላል፡፡ ለዚህ ድምዳሜ ያበቃኝ በዚያው ምዕራፍ ውስጥ ሳላይሽ የምትባለው ገፀባህሪ የምትወረውረው ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ "ይመስላት ነበር መታለልና ማታለል <u>አረንጓዴነት</u>ና መሃይምነት፡፡" (አዳም፣2008፣ 148) (አጽንዖቱ የኔ ነው) በዚህ አውድ ውስጥ አረንጓዴነት የዋህነት፣ አለመብሰል፣ ለጋነት የሚል ፍቺ አለው፡፡

ምዕራፍ ሦስት በጥቁር ተወክሏል፡፡ ይህ ምዕራፍ የምኒልክ ሕይወት የሚተረክበት ክፍል፡፡ ለምን በጥቁር ተወከለ ብለን ስንጠይቅ ወርቁ የሚባለው፣ የምኒልክን የሕይወት ታሪክ ያሳተመው ገጸባህሪ "በመጨረሻም ጥቁር አልኩት፡፡ ምክንያቱም የምኒልክ ፍቅረኞች ደጋግመው ጥቁር ልብሶች (ሹራብ፣ ቀሚስ፣ ሸሚዝ፣...ወዘተ) መልበሳቸውን ስለሚናገር ነው፡፡ ከዚህ ተነስቼ የምኒልክ ልጅነት ጥቁር ነበር..." (አዳም፣2008፣279) የዚህ ምዕራፍ የቀለም ውክልና በጥቂቱም ቢሆን ለልብወለዱ የሚያበረክተው ጭብጣዊ ፋይዳ አለ፡፡ በኛ ልማድ ውስጥ ጥቁር በሀዘን፣ በማይምነት ይወከላል፡፡ ውክልናውም የምኒልክን ልጅነት መራራነት ያሳያል፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የምኒልክ ልጅነት በነፊያሜታ፣ ቤላና መሰሎቻቸው የተመረዘ ነበር፡፡  ውክልናውም ይህንን ማጉላት ነው፡፡

ምዕራፍ አራት በሰማያዊ ተወክሏል፡፡ ለምን በሰማያዊ ተወከለ? ሰማያዊ፡ የ ዘ ድሬክ ካፌ ሕንጻና በረንዳ ዣንጥላዎች ቀለም ነው፡፡ ምናልባትም ውክልናው ከዚህ የዘለለ ትርጉም ያለው ይመስላል፡፡ ይህ ምዕራፍ መንኮቢያው (ስንዝሮ) ብቅ የሚልበት ምዕራፍ ነው፡፡ መንኮቢያው ከተረት ፍጡርነቱ ባሻገር መንፈሳዊ ውክልናም አለው፡፡ መንኮቢያው ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ከሀገር ሀገር ሲንከራተት የኖረ መለኮታዊ ባሕርይ ያለው ፍጡር ነው፡፡ የሰማያዊ ቀለሙም ውክልና ይህንን ለመግለጽ ይመስላል፡፡

ምዕራፍ አምስት በቢጫ ተወክሏል፡፡ ቢጫ በምንኩስናው ዓለም ማርጀትን መወየብን ያመለክታል፡፡ ታድያ ለምን በቢጫ ተወከለ? በዚህ ክፍል ስለ ቢጫ ቀለም የተነሳው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ቢጫ፡ የተኮላ አሳዳጊ የአቶ ደጃዝማች ጆቴ ኩምቢ ቮልስዋገን መኪና ቀለም ነው፡፡ ምናልባትም ይሄ የዘውዳዊውን ስርዓት ማርጀትና ስንብት የሚጠቁም ይመስላል፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመጨረሻ ጊዜ ከቤተ መንግስት ሲወሰዱ የተሳፈሩበት ተሽከርካሪ ቮልስዋገን መሆኗን ልብ ይሏል፡፡ ቢጫ አንድም የመወየብ የማርጀት ተምሳሌትነት ሲኖረው በሌላ በኩል ደግሞ የተስፋ፣ የአዲስ ጅማሮ ውክልና አለው፡፡

ምዕራፍ ስድስት በወርቅ ተወክሏል፡፡ ወርቅ፡ ስንዝሮ ወይም መንኮቢያው ለምትክ የወርቅ ስጦታ ያበረከተበት ምዕራፍ ነው፡፡ መንኮቢያው ምትክን “በቅንድብሽ ፀጉር ልክ ወርቅነትሽ ተጽፏል” (አዳም፣2008፣ 690) ብሏታል፡፡ ይህ ስለ ምትክ (ስለ ሀገራችን) የተነገረ ነው፡፡ እንደ ሙገሳም እንደ ትንቢትም ሊቆጠር ይችላል፡፡ ሙገሳ ስንልም የሀገሪቱን ወርቅነት፣ ለምለምነት፣ ...ለመግለጽ የታሰበ ነው፡፡ ትንቢት ስንል ደግሞ ዘግይቶም ቢሆን ለሚመጣው ብሩህ ዘመን ንግር ነው፡፡

ምዕራፍ ሰባት በቀይ ተወክሏል፡፡ ቀይ የሻገር ሬስቶራንት የሰራተኞች “ባጅ” ቀለም ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ይህ ምዕራፍ ዘውዲት ራሷን ያጠፋችበት፣ የደም ስሯን በምላጭ የተለተለችበት ምዕራፍ ነው፡፡ ታድያ ቀይ ቀለም ለጭብጡ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ቀይ ቀለም በልጅነቷ ጸንሳ ለተገፋችው ዘውዲት መሰሎቿ መታሰቢያነት የተወከለ ሲሆን የንጹህ ደም በከንቱ መፍሰስን የሚገልጽ ይመስላል፡፡

የመጨረሻው ምዕራፍ፡ ምዕራፍ ስምንት በነጭ ተወክሏል፡፡ ነጭ፡ ቀለም የሠላም ምልክት ነው፡፡ ነጭ የብርሃን ምሳሌ ነው፡፡ ነጭ፡ ምትክ ማኩታን ስትወልድ ከማህጸኗ የወጣው ወጋጋን ምሳሌ ነው፡፡ ነጭ፡ በዓለማቀፋዊ ውክልና የሠላም ምልክት ነው፡፡ ምናልባትም ወደፊት የሚመጣውን የሀገራችንን እጣፋንታ የሚጠቁም ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በኛ ልማድ ውስጥ ነጭ የደስታና የተድላ ምልክት ነው፡፡ "ከሚያሰምጠኝ ውሃ ውስጥ ቀና ስል እስከ አድማስ የተዘረጋ የደረሰ የገብስ እርሻ አያለሁ፡፡መስኩ እንደ ወርቅ ባሕር ይርገበገባል፡፡ የገብስ እርሻ አይቼ አላውቅም፡፡ ነጫጭ አዕዋፍ እርሻው ውስጥ ይርመሰመሳሉ ፡፡ልይዛቸው እጄን ስዘረጋ ክንዴ ላይ ቆመው ከመዳፌ ላይ ጥሬ መልቀም ጀመሩ፡፡(አዳም፣2008፣ 926) ሰፊው የደረሰ የገብስ ሰብል ጥጋብና ተድላን ይወክላል፡፡ በእጆቿ ጥሬ የበሉት ነጫጭ አእዋፋት ደግሞ የሠላምና የፍቅር ተምሳሌት ናቸው፡፡ የልብወለዱ ታሪክ 1987 ዓ.ም ሰኔ ወር ጀምሮ መስከረም ሲጠባ መጠናቀቁም አገራችን ወደ አዲስ የዘመን ምዕራፍ እየተሸጋገረች መሆኑን ያበስራል፡፡ “የስንብት ቀለማት” በአንድ በኩል የአንድ ትውልድ ስህተትና ውድቀት የሚተረክበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ ትውልድ ትንሳኤ የሚበሰርበት የራሱ ብሉይና ሀዲስ ያለው ሥራ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. ማጠቃለያ

ጥናቱ በ2008 ዓ.ም. በታተመው የአዳም ረታ "የስንብት ቀለማት" ረጅም ልብወለድ የጭብጥ አቀራረብን ፈትሿል። ጥናቱ የተጠቀመው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ሲሆን፣ መዛግብት ወይም ሠነድ ፍተሻ ደግሞ በመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴነት አገልግሏል። ነገረ ህላዌ (existentialism)በመረጃ መተንተኛ ዘዴነት ተጠቅሟል።

የስንብት ቀለማት አብይ ጭብጥ የፍጥረታት ሁሉ የመጨረሻው ግብ ሞት መሆኑን ማርዳት ነው። በንዑሳን ጭብጥነት ደግሞ የ"ያ ትውልድ" ስህተቶች፣ የመበዳደል አዙሪትና ጭላንጭል ተስፋዎች የሚሉ ሦስት አብይት ርዕሰ ጉዳዮች ተነስተዋል።

የ "ያ ትውልድ" ስህተቶች የወጣትነታቸውን ጊዜያት በአስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹና ሰባዎቹ ያሳለፉ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የነበራቸው የዘመኑ ወጣቶች የፈጸሟቸውን ስህተቶች ዳስሷል።

ሌላኛው ንዑስ ጭብጥ "የመበዳደል አዙሪት" ነው። ይሄ ደግሞ በልብወለዱ ውስጥ ስጋ ነስተው የሚንቀሳቀሱ ገፀባህሪያትን ግጭትና የግጭታቸውን መንስኤ፣ እንዲሁም ግጭታቸው ያስከተለውን በትንተናው ተመልክቷል። "የስንብት ቀለማት" የጊዜ መቼት ከስልሳዎቹ መጀመሪያ እስከ ሰማንያዎቹ መጨረሻ ድረስ ባለው የጊዜ ሀዲድ ላይ የተዘረጋ ሲሆን አንዳንድ ገጸባህርያት ከሀያ ዓመት በላይ የዘለቀ ቁርሾ አላቸው። "የስንብት ቀለማት" ውስጥ ሁሉም ገጸባህሪያት በሆነ መንገድ የበዳይነትና ተበዳይነት ሚና አላቸው። ጋዜጠኛው ከያኒውን፣ ፖለቲከኛው ሲቪሉን፣ ዲያስፖራው ያገር ቤቱን ሰው፣ ሹመኛው ወታደሩን፣...ሲበድል ታይቷል።

ሌላኛው ንዑስ ጭብጥ "ጭላንጭል ተስፋዎች" ነው። "ጭላንጭል ተስፋዎች" ከተወሳሰበው የስንብት ቀለማት ዓለም ውስጥ የሚታዩ ጭላንጭል ተስፋዎችን ያሳያል። ግጭቶች ይረግባሉ። ይገፋፉ የነበሩ ገፀባህርያት ልጆች ይዋደዳሉ። መልካሞች ይካሳሉ። ክፉዎች ይወድቃሉ። ጭላንጭል ተስፋዎች ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የ "ያ ትውልድ ስህተቶች" እና "የመበዳደል አዙሪት" በሚሉ ርዕሶች ከተዳሰሱት ጉዳዮች ጋር እየተንሰላሰለ ታይቷል። "የስንብት ቀለማት" አንድም የስልሳዎቹን ትውልድ ከነበረው ንቁ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ስንብት የሚጠቁም ሲሆን

በሌላ በኩል ደግሞ የአዲሱን ትውልድ ትንሳዔ ያበስራል። ይህ እንደ ጥሩ ጎን ሊነሳ የሚችል ስለሆነ እንደ ተስፋ ጭላንጭል ይታያል። ይህ ሲባል ግን ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ ነው ማለት አይደለም። ተስፋችንን ወደ ጭላንጭል የሚቀየሩ አንዳንድ ጉዳዮችም አሉ። ለምሳሌ የዘመኑ የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም ከደርግ የፖለቲካ ርዕዮት ዓለሞ ፍጽሞ የተለየ ነው። የፖለቲካ መዋቅሩ ብሔር ተኮር ነው። ይህ ዓይነቱ ፖለቲካዊ ርዕየት ዓለም ደግሞ ዜጎች በተወሰነ መንገድ ከፖለቲካ ውጪ መሆን እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል። ይህ ደግሞ አስተማማኝ የሆነ ዘላቂ ስላም ለመኖሩ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ እንዳይኖረን ያደርጋል። ሌላኛው ተስፋችን ላይ ጥቁር ጥላ የሚያጠላበት የወጣቶቹ ከያኒያን ጠበቃ የሆኑት አቶ ዮሐንስ ወላይሶ ዜና እረፍት ነው። አቶ ዮሐንስ ወላይሶ አደጋ ገጥሚቸው ይሁን በሰው እጅ ተገድለው በግልጽ የተቀመጠ ነገር የለም። ይህም በአደጋው ዙሪያ ተጨባጭ መረጃ እንዳይኖረን ያደርጋል። ይህም ተስፋችንን ወደ ጭላንጭል ከሚቀይሩ የልብወለዱ ታላላቅ ክስተቶች መካከል አንዱ መሆኑ ታይቷል። ሌላኛው በስንብት ቀለማት ውስጥ የታየው ደማቁ የተስፋ ጭላንጭል የአገራችን ተምሳሌት የሆነችው ምትክም አዲሱን የስንዝሮን ዘር ማኩታን መጸነሷ ነው። ይሄም አንድም ኢትዮጵያ ለተጨማሪ አምስት ሺህ መቶ ዓመታት ወደሚያቆያት አዲስ የዘመን ምዕራፍ እየተሸጋገረች ለመሆኑ ማሳያ ነው። የልብወለዱ ታሪክ 1987 ዓ.ም ሰኔ ወር ጀምሮ መስከረም ሲጠባ መጠናቀቁም አገራችን ወደ አዲስ የዘመን ምዕራፍ እየተሸጋገረች መሆኑን ያበስራል።

እነውቤ ታደገ ሥነፅሁፍ፣ ፅንሰ ሐሳብ፣ታሪክና ጒስ በሚለው መፅሐፋቸው እንዲህ ብለውናል". . በአማርኛ ረጅም ልብ ወለድ ታሪክ የስንብት ቀለማት በገፅ ብዛት ወደር የሌለው ግዙፍ ረጅም ልብወለድ ነው።ትዳርን፣ወጣትነትን ፣ሀብትን ፣ድህነትን ፣ሴትነትን፣ኪነትን በመሳሰሉ ቁምነገሮችና ላይ በመመርኮዝ የገፀ ባሕርያትን ሥነ ልቦናዊ ዐለም እንደወረደ አቅርበዋል።አዳም ረታ በእነዚህ ሥራዎቻቸው ጥቃቀን የሚመስሉ ጉዳዮችን በማንሳት ትልቅነታቸውን አመልክተው በመንፈስ ዝንጋኤ በአያሌው መመታታችን ለመጠቆም ችለዋል።(214)

በአጠቃላይ ይህ መፅሐፍ በሌሎች ዲሲፕሊኖችም ሊጠና ይችላል።

# የተጠቀሱ ጽሑፎች


አዳም ረታ::(2008):: የስንብት ቀለማት:: አዲስ አበባ፣ ሮኖቦት አታሚዎች::

አበባው አቢ:: (1998):: የጭብጥ ትንተና በሙሽጥ ረጅም ልብወለድ ላይ ::(ቢ.ኤ.ያልታተመ)::አዲስ አበባ::አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ::

ጌታቸው በለጠ:: (2004):: የጥበባት ጉባኤ:: አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት ::

ጌታቸው በለው:: (1976):: በድህረ ፋሽሽት ዓመታት በተፃፉ የአማርኛ ልብወለዶች ውስጥ ተደጋግመው የሚታዩ ጭብጦች ::(ቢ.ኤ. ያልታተመ)::አዲስ አበባ::አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ::

ተስፋዬንጉሴ:: (1995)::የጭላንጭልልብወለድታሪክየጭብጥትንተና::(ቢ.ኤ.ያልታተመ)::አዲስአበባ ::አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ::

ደስታ ተክለወልድ:: (1970):: ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት:: አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ዘሪሁን አስፋው::(1992):: የስነፅሁፍ መሰረታዊያን:: አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት ::1992::

ውቤታደገ፣ደምስመሸሻና የሺዋስ ዓለሙ::(2013)::ሥነፅሑፍ፣ፅንሰሐሳብ፣ታሪክና ኂስ::ደሴ፣ኢትዮጵያ::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: (1993)::አማርኛ መዝገበ ቃላት:: አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ያለው እንዳወቅ:: 2006):: ምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር:: አዲስአበባ፣ ንግድማተሚያ ድርጅት::

Aklilu,D.(2010). Existenialism In the selected creative works of Adam Reta.(MA thesis)Unpublished.Addis Abeba. Addis Ababa University.

Carlsen, G.(1979). Themes and writers. USA: Mc. Graw-Hill book Company, Inc.

Culler, J..(1997). Introduction to literary theory: A very short introduction. New York: Oxford university press.

Daiches, D. (1981).Critical Approaches to Literature. Longmans, Greenock London, New York:Toronto.

Drefus,H&Wrathall.M.(2006).(Eds).ACombaniontophenomenology&Existentialism.Australia:Black Well Publishing.

Eagleton, T. (1943).Literary Theory. An Introduction. London; Black Well Publications .

- - - .(1990).The Significance of Theory (Black Well, Oxford,)

Edgar. H.(1963).Discovering Theme &Structure In The Novel. The English Journal Vol. 52. No. 7 pp. 506-511 (6 pages) published by. National Council of Teachers of English

Eliot,S.&W.R.Owens.(1998).(ed.). A Handbook to Literary Research. Published in USA&Canada by Routledge 29 west 35th stree, New York.

Flynn,T.(2006).Existentialism.Avery Short Introduction.Oxford Universty Press.

Greg.T.R.Perrines(2016) Literature,Structure,Sound and sense.13th ed.printed inUSA.

Gorden.H.(1999).(ed.).Dictionary of Existentialism.USA:Green Wood Publishing Group.

Hart, C.(1998) Doing a literature review. London: SAG PUBLICATIONS. .

Hawthorne, J.(2001) A Glossary of Contemporary Literary Theory. 4th ed. London. Arnold Publication.

Hudson, W..(1913).An Introduction to the study of Literature. George G. Harrap&company. Portsmouth Street Kingsway W.C.

Kathry.A.(1992).Constructing the theme of a story.vol.2 No.2.Before Middle Language Arts For Children In The Upper Elementary School.Published by National Council of teaching.pp.106-111.

Kenny ,W.(1996).How to analyze fiction.New York:Monarch Press.

Mulugeta, A.(2017). Adam Reta's Colors of Adios; book reviews.

Michael M. (2000).Theory of the Novel. A Historical Approach. The Johns Hopkins Universty Press. Baltimore &lLondon .

Quinn,E.(2006)..A dictionary of literary and Thematic Terms ,2nd.ed.Facts on File .An Imprint of Infobase Publishing.

Reinhard .K.(1952).The existentialist revolt.USA:The Bruce Publish in company Milk Waukee.

Syed, M. (2010).The Craft of Language and Literary Research. Atlantic Publishers & Distributors Ltd.,

Wellek, R. and Austin w. (1942)Theory of literature. New York: Harcourt.

Wolfreys, J. (2006). Key conepts in Literary Theory. 2nd ed. Edinburgh: Edinburgh Universty PressLtd,